
# የአካባቢ ሳይንስ

## የማስተማሪያ መጽሐፍ



# አካባቢ ሳይንስ

# ማስተማሪያ መጽሐፍ

# አንደኛ ክፍል

# ማ ው ጫ

ርዕስ ገጽ


ክፍል ትምህርት አንድ

**1** እኛነታችን---------------------------------------------------------- **1**

1.1. ውጫዊ የሰውነት ክፍሎቻችን-------------------------------- 1

1.2. መሰረታዊ ፍላጎቶቻችን-------------------------------------- 5

1.3. በተደጋጋሚ የሚያጠቁን በሽታዎች---------------------------- 11

1.4. አምስቱ የስሜት ሕዋሳት-------------------------------------- 20

ክፍል ትምህርት ሁለት

2. ቤተሰቦቻችን ------------------------------------------------------ 32

2.1. የቤተሰብ አባላት---------------------------------------------- 32

2.2. የቤተሰብ መሠረታዊ ፍላጎቶች---------------------------------- 39

2.3. የቤት ቁሳቁሶች ------------------------------------------ 44

ክፍል ትምህርት ሦስት

**3.** ትምህርት ቤታችን---------------------------------------------------- 52

3.1. የትምህርት ቤታችን ግቢ ------------------------------------- 52

3.2. የትምህርት ቤት ሕግና መመሪያ ማክበር ----------------------- 56

3.3. ጥሩ /መልካም/ የሆኑ የግል ግንኙነቶች ------------------------- 58

3.4. የመንገድ ላይ ጥንቃቄ ---------------------------------------- 59

3.5. በትምህርት ቤታችን የምናደርጋቸው እንቅስቃሴዎች-------------- 62

ክፍል ትምህርት አራት

**4.** ቀበሌያችን መንደራችን 64

4.1. የቀበሌያችን መገኛ------------------------------------------- 65

4.2. በአካባቢያችን የሚገኙ ሕይወት የሌላቸው ነገሮች------------------ 66

4.3. በአካባቢያችን የሚገኙ ሕይወት ያላቸው ነገሮች -------------------- 72

4.4. በአካባቢያችን የሚደረጉ የተለመዱ እንቅስቃሴዎች----------------- 81

4.5. መጓጓዣዎች-------------------------------------------------- 85

# መ ግ ቢ ያ

ይህ የመምህሩ መምሪያ መጽሐፍ እንደገና ተሻሽሎ በተዘጋጀው ሲለበስ ተመስርቶ የቀረበ ነው።

አላማውም መምህሩ በተማሪው መማሪያ መጽሐፍ ላይ በመመርኮዝ ትምህርቱን በሚፈለገው የተማሪ መልካም ለውጥ በእውቀት፤ ክህሎትና አመለካከት ሊያመጣ የሚችልበትን መንገድ ለመጠቆም ነው።

የአንደኛ ክፍል አካባቢ ሳይንስ በአራት ክፍለ ትምህርቶች የተከፈለ ሲሆን የሕብረተሰብ ሳይንስ፤ የስነዜጋና ሥነምግባር ትምህርትን፤ የእርሻ ፤ የእጅ ሥራና የጤና ትምህርትን በማካተት ተማሪዎች ስለአካባቢያቸው ያላቸውን ግንዛቤ፤ ክህሎትና አስተሳሰብ ለውጥ የሚያሰጨብጣቸው መሆን አለበት። በአጠቃላይ ይህ የመምህሩ መምሪያ በሚከተሉት ነጥቦች ላይ ያተኩራል።

በየክፍለ ትምህርቱና በዋና ዋና ርዕሶች መጀመሪያ ላይ ተማሪው ምን እንደሚጠበቅበት ይገልፃሉ።

ለመምህሩ የማስተማር መማር ዘዴዎች አቅጣጫን ለማስያዝ የሚጠቁሙ ሲሆኑ በሌላበኩል ተማሪዎች የትምህርቱን ይዘት ምን ያህል ተረድተዋል? የሚለውን ጥያቄ በተለያዩ ችሎታ /የማንበብ፤ የመጻፍ...../ የሚመልሱ መገምገሚያ ወይም መመዘኛዎች ተቀምጠዋል። በተጨማሪ የትምህርቱን ይዘት ተጨባጭ እንዲሆን እንደየትምህርት ቤቱ አካባቢ ሁኔታ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን ማዘጋጀትና መጠቀም እንደሚኖርባቸውና አካባቢያቸው ራሱ እውን የትምህርትመርጃ መሣሪያነት መጠቀም እንደሚችሉ መገንዘብ ያስፈልጋል።

# ክፍለ ትምህርት አንድ

## 1. እኛነታችን

የተመደበለት ክፍለ ጊዜ ብዛት 57

አጠቃላይ አላማዎች

ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቅ ውጤት፡- ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፡-

- ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች የሚባሉት የትኞቹ እንደሆኑ ለይተው ያሳያሉ፤ የእየንዳንዱን ስምና አገልግሎት ይናገራሉ።
- የሰውን ልË ሦስት መሰረተዊ ፍላጐት ይዘረዝራሉ፤ የእየንዳንዱንም ጠቀሜታ ይገልፃሉ።
- በአከባቢያቸው የተለመዱ በሽታዎችን ይዘረዝራሉ፤ የመከላከያ ዘዴዎችንም ይዘረዝራሉ።
- አምስቱን የስሜት ሕዋሳት ስምና አገልግሎት ይገልፃሉ፤ የስሜት ሕዋሳትን በመጠቀም ተገቢ ፍተሻ የካሂዳሉ።
- ቀለል ባሉ ተግባራት አማካይነት የብርሃን፤ የድምጽ ፤ የቀለም፤ የጣእምና የሽታ ምንጮችን ይለያሉ።

በአጠቃላይ በክፍል ትምህርቱ ሂደት ሳይንሣዊ የመማር ዘዴን ተግባራዊ ያደርጋሉ፤ ጥልቅ ምልከታ /ፍተሻ/ ያደርጋሉ፤ ይጠይቃሉ፤ ሃሣብ ለሃሣብ ይለዋወጣሉ፤ በጋራ በመረዳዳት ይሰራሉ።

### 1.1. ውጫዊ የሰውነት ክፍሎቻችን

የተመደበለት ክፍለ ጊዜ ብዛት 10

ዝርዝር አላማዎች

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፡-

- ውጫዊ የሰውነት ክፍሎቻቸውን ይናገራሉ።
- ውጫዊ የሰውነት ክፍሎቻቸውን ያሳያሉ።
- ውጫዊ የሰውነት ክፍሎቻቸውን አገልግሎት ይናገራሉ።

ዝርዝር ይዘት

1.1.1 ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች

1.1.2 የውጫዊ የሰውነት ክፍሎች አገልግሎት

- ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች መጠበቅ
    - እግርን መታጠብ
    - ጥፍርን በየጊዜው መቁረጥ
    - ጥርስን በየቀኑ ማጽዳት
    - የአፍንና የጆሮን ንጽሕና መጠበቅ
    - ፀጉርንና ገላን በየጊዜው መታጠብ

የማስተማር መማር ዘዴዎች

መምህር ተማሪዎች ስለ ውጫዊ አካል ክፍሎቻቸው በይበልጥ እንዲያውቁ የሰው ስእል ወይም ሞዴል ወይንም ደግሞ የራሳቸውን ውጫዊ የሰውነት ክፍሎችን እንዲለዩና በመማሪያ መጽሐፍ ላይ በተጠየቁት ጥያቄዎች እና በተቀመጠው ስእል መሰረት ጥንድ ጥንድ ሆነው ጥየቄዎቹን እንዲሰሩ ማድረግ ። በተጨማሪ ውጫዊ የአካል ክፍሎቻቸውን በመንካትና ስማቸውንም በመጥራት እንዲየሳዩ ማድረግ ትምህርቱን ይበልጥ ተጨባጭ እንዲሆን ያግዝዎታል።

ተማሪዎች የሰውነት ውጫዊ ክፍሎችን አገልግሎት እንዲገልጹ በጨዋታ መልክ ማከናወን ይቻላል። ይኸውም አንድ ተማሪ የሰውነት ክፍሎችን አገልግሎት እንዲገልጽ ማድረግና ሌሎች የክፍሉ ተማሪዎች ስለየትኛው የሰውነት ክፍል እንደተገለፀ እንዲገምቱ ማድረግ።

መምህር ተማሪዎች የሰውነት ክፍሎችን ንጽሕና አለመጠበቅ የሚየስከትለውን ጉዳት አስመልክቶ የደረሰባቸው ጉዳት ካለ በምሳሌ መልክ በማቅረብ እንዲሁም በቀረቡት ምሳሌዎች ላይ እንዲወየዩና የራሳቸውን ምሳሌዎች እንዲያቀርቡ ማድረግ ጠቀሜታው የጐላ ነው። ተማሪዎች የሰውነት ክፍሎቻቸውን ንጽሕና አጠባበቅ ተግባራት እንዲለማመዱ ማድረግ ለምሳሌ፡- እንጨት መፋቂያዎችን በመጠቀም ጥርሳቸውን እየፋቁ እንዲለማመዱ ማድረግም የቀረበውን ይዘት ተግባራዊ እንዲየደርጉት የግዝዎታል።

ትምህርት መር É መሳሪያዎች

- የሰውን ውጫዊ አካልክፍሎች የሚያሳይ ስእሎች
- ሞዴሎች
- ተማሪዎች የራሳቸውን ተጨባጭ አካል ክፍሎች በመጠቀም
- ንጹሕ ማበጠሪያ
- ንፁህ ውሃና ሳሙና

- ባሕላዊና ዘመናዊ የጥርስ ንጽሕና መጠበቂያ ቁሶች
- ዘመናዊ የጥፍር መቁረጫ

ግምገማና ምዘና / ግምገማና ክትትል/

- ተማሪዎች በስእል አማካኝነት የሰው ውጫዊ አካል ስያሜ እንዲጠሩ መጠየቅ።
- የራሳቸውን የውጫዊ አካላት ክፍሎቻቸውን እንዲያመለክቱ የቃል ጥያቄ መስጠት።
- የአካል ክፍሎችን ንጽሕና አጠባበቅ ዘዴዎች እንዲዘረዝሩ መጠየቅ።
- የእያንዳንዱ የአካል ክፍሎቻቸውን አገልግሎት ዘርዝረው እንዲናገሩ መጠየቅ።
- የአካል ክፍሎቻቸውን ንጽሕና አጠባበቅ ልምምድ ላይ አመቺ ጊዜ በመያዝ ክትትል ማድረግ።

የመልመ **É 1.1.** መልሶች

ሀ. ሐ.3

መ.4

ሠ.5

ረ.6

ሰ.7

ሸ. 8

ቀ. 9

በ.10

ተ.11

ለ. ሀ.12

ለ.13

ሐ.14

መ.15

ሠ. 16

ረ. 17

ሰ. 18

ሸ. 19

ቀ. 20

በ. 21

ተ. 22

ቸ. 23

የመልመ É 1.2 መልሶች

ሀ. 1. እውነት

2. ሐሰት

3. እውነት

ለ. 4. ለ

5. መ

6. መ

## 1.2. መሰረታዊ ፍላገቶቻችን

የተመደበለት ክፍለ ጊዜ ብዛት 8

ዝርዝር አላማዎች

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፡-

- ሦስቱ የሰው ልጅ መሰረታዊ ፍላጐቶች ምን ምን እንደሆኑ ይዘረዝራሉ።
- ሦስቱ የሰው ልጅ መሰረታዊ ፍላጐቶች ጠቀሜታ ምን ምን እንደሆኑ ይገልፃሉ።

ዝርዝር ይዘት

የሰው ልጅ መሰረታዊ ፍላጐቶች

- ምግብ
- መጠለያ
- ልብስ

የሰው ልጅ መሠረታዊ ፍላጐቶች ጠቀሜታ

የማስተማር መማር ዘዴዎች

መምህር ተማሪዎች የሰው ልጅ መሰረታዊ ፍላጐቶች ምን ምን እንደሆኑ በቡድን ተከፋፍለው እንዲወያዩ አድርገው የማጠቃለያ ሃሣብ ይስጧቸው ።

ምግብ ልብስና መጠለያ የሰው ል Ë መሰረታዊ ፍላጐት መሆናቸውን በመግለጽ የተለያዩ ምግቦችን ልዩ ልዩ የልብስ አይነቶችንና የተለያዩ ቅርጽ ያላቸውን መጠለያዎች ምሳሌ እንዲሰጡ ማድረግ ከእነዚህም ሶስት መሰረተዊ ፍላጐቶች መካከል አንዱ ባይሟላ ምን ሊያጋጥማቸው እንደሚችል እንዲወያዩ ማድረግ።

የትምህርት መር É መሳሪያዎች

- ስእሎች
- ሞደሎች
- ፎቶግራፎች
- ፓስተሮች
- ቻርቶች

ግምገማና ምዘና /ግምገማና ክትትል/

- የሰው ልጅ መሠታዊ ፍላጐቶች እንዲዘረዝሩ የቃል ጥያቄዎችን መጠየቅ።
- ስለ ሰው ልጅ መሰረታዊ ፍላጐቶች የተለያዩ መልመ É ዎችና ሙከራዎችን መስጠት።

ሀ/ ምግብ

ዝርዝር አላማዎች

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ ፡-

- ምግብ ለሰው ልጅ የሚሰጠውን ጥቅም ያብራራሉ።
- የምግብ መለያ ባሕሪያትን ያስረዳሉ።

- ምግቦችን በአይነታቸው ይመድባሉ።

ዝርዝር ይዘት

የምግብ ጥቅም

- ለጤንነት
- ለተስተካከለ እድገትና ለአካል ግንባታ
- ለሃይልና ጥንካሬ /ብርታት/

የምግብ መለያ ባህሪያት

- ጣእምና መአዛ
- ፈሳሽ ወይም ጠጣርነት
- ቀለም

የማስተማር መማር ዘዴዎች

የሰው ልጅ ምግብ የሚያስፈልገው ሰውነቱ እንዲያድግ፤ ጥንካሬ እንዲኖረውና ኃይል እንዲሰጠው መሆኑን ለተማሪዎች መግለጽ።

ተማሪዎች የሚመገቧቸውን ምግቦች እንዲዘረዝሩ /የምግብ አይነቶችን ስም እንዲናገሩ/ማድረግ።

በጣም የሚወዱት የምግብ አይነት የትኛው እንደሆነ መጠየቅ። በተጨማሪም በክፍል ውስጥ በቡድን በቡድን ተከፋፍለው በሚያውቁት የምግብ አይነት ላይ ተማሪዎቹ እንዲወያዩ መርዳት፤ በመቀጠልም ምግቦች በባሕሪያቸው የተለያዩ መሆናቸውን እንዲያብራሩ ማድረግ። ይኸውም በቀለም ፤ በመአዛ፤ በጣእም በጠጣርነትና በፈሳሽ እንዲመድቧቸው በማድረግ ትምህርቱን መቋጨት።

የትምህርት መር É መሣሪያዎች

- የተለየዩ የምግብ አይነቶችን የሚያሳዩ ፒስተሮች፤ ስእሎች
- በምግብ እጥረት በሚመጣ በሽታ የተያዘ የሰው ስእል /ከመማሪያ መጽሐፍ ሥእል 1.7 ን ይመልከቱ/።
- ለጤንነት የሚረዱ የምግብ አይነቶች የሚያሳይ ስእሎች /ሥእል 1.6 ን ይመልከቱ/
- ለእድገት ለአካል ግንባታ የሚረዱ ምግቦች የሚያሳዩ ስእሎች /ሥእል 1.8 ን ይመልከቱ/

- ለብርታትና ለጥንካሬ የሚረዱ ምግቦችን የሚያሳይ ስእል /ከመማሪያ መጽሐፍ ሥእል 1.9 ን ይመልከቱ/

ግምገማና ምዘና /ግምገማና ክትትል/

- የምግብን ጥቅም እንዲያብራሩ የክፍል መልመ É መስጠት።
- የምግብ መለያ ባሕሪያትን እንዲዘረዝሩ መጠየቅ።
- ምግቦችን በባሕሪያቸውእንዲመድቡ የቃል ጥያቄ ማቅረብ።

ለ. ልብስ

ዝርዝር አላማዎች

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ ፡-

- ልብስ ለምን እንደሚጠቅም ይገልፃሉ።
- ልብስ ከምን ከምን እንደሚሰራ ያስረዳሉ።
- የልብሶችን ባሕሪያት ይገልፃሉ።
- በክረምትና በበጋ የሚለበሱ ልብሶችን ይለያሉ።

ዝርዝር ይዘት

- የልብስ ጥቅም
  - ከብርድ፤ ከፀሐይና ከዝናብ ለመከላከል፣
  - ውበትን ለመጠበቅ።
- ልብስ ከምን ይሰራል?
  - ጥጥ
  - ሱፍ
  - ቆዳ
  - ናይለን
- የልብስ ባሕሪያት
  - ለስላሳ
  - ሻካራ
- የልብስ ቀለማት

- ጥቁር፣
- ነጭ፣
- ቀይ፣ ወዘተ.

የማስተማር መማር ዘዴዎች

መምህር ተማሪዎች ልብስ ለምን እንደሚጠቅም እንዲናገሩ መጠየቅ፤ ልብስ እንደየአካባቢያችን የአየር ሁኔታ /ብርድን፣ ቅዝቃዜን፣ ፀሐይ ብርሃንንና ዝናብን/ ለመከላከል፣ አካላችንን /ገጽታችንን/ ለመሸፈንና አካላዊ ቅርፃችንን ለማሳመር የሚያስፈልግ መሆኑን መግለጽ። ተማሪዎች የለበሷቸው ልብሶች ከምን ከምን እንደተሰሩ እንዲወያዩ ጥያቄዎችን ቀድመው በመጠየቅ እያንዳንዱ ተማሪ እንዲሳተፍ ማድረግ። ከጥጥ፣ ከሱፍ፣ ከቆዳና ከናይለን የሚሰሩ ልብሶችን ለይተው እንዲናገሩ ማድረግ። እነዚህም ጥሬ እቃዎች የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ የሆኑ ጥሬ እቃዎች መሆናቸውን ማስረዳት።

ልብስ ልዩ ልዩ ባሕሪያት እንዳለው በመጠቆም ተማሪዎች እንዲወያዩ መርዳት፤ ለስላሳና ሻካራ ልብሶች እንደሆኑና መቼ መቼ እንደሚለበሱ ጨምረው በመግለፅ ማስረዳት። ተማሪዎች ልብሶች በቀለማት እንደሚለያዩ በክፍል ውስጥ የለበሱትን ልብስ የቀለም አይነት እንዲናገሩ በመጠየቅ ትምህርቱን መቋጨት ያስፈልጋል።

የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

- የተለያዩ ቁርጥራጭ ጨርቆች ናሙናዎች እንዲያመጡ ማድረግ።
- የተለያዩ ስእሎች /ከመማሪያ መጽሐፍ ሥዕል 1.11 ይመልከቱ/
- ሞዴሎች

ግምገማና ምዘና /ግምገማና ክትትል/

- የተለያየ የጨርቅ ቁርጥራጮችን በተሰሩበት አይነት /ከጥጥ፤ ከናይለን፤ ከሱፍ ከቆዳ/ በማለት አይነታቸውን እንዲመድቡ ማድረግና መከታተል።
- የልብሶችን ባሕሪያት እንዲገልፁ መጠየቅ።
- የክፍሉ ተማሪዎች የለበሷቸውን ልብሶች ቀለማት እንዲገልፁ የቃል ጥያቄ ማቅረብ።
- የልብሶችን ጥቅም እንዲዘረዝሩ መጠየቅ።

- በክረምትና በበጋ የሚለበስ የልብስ አይነቶችን እንዲለዩ በቃል መጠየቅ።

ሐ/ መጠለያ

ዝርዝር አላማዎች

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ ፡-

- የመጠለያን ጥቅም የስረዳሉ።
- በአካቢያቸው የመጠለያ ቤቶች ከምን ከምን እንደሚሰሩ ይለያሉ።

ዝርዝር ይዘት

የመጠለያ ጥቅም

- ከቅዝቃዜና ከዝናብ፣
- አደጋ ከሚያስከትሉ የዱር እንስሳት ለመከላከል።

መጠለያ ቤቶች የሚሠሩበት ቁሳቁሶች

- ሳር
- እንጨት
- ቆርቆሮ
- ብሎኬት
- ብረት
- ሲሚንቶ
- አሸዋና የመሣሠሉት ናቸው።

የማስተማር መማር ዘዴዎች

መምህር ተማሪዎችን የሰው ልጅ መጠለያ ለምን እንደሚያስፈልገው መጠየቅ፤ መጠለያ እንደየአካባቢው የአየር ሁኔታ /ከብርድ፤ ከፀሐይ ብርሃን ጨረር፣ ከዝናብ፤ ከነፋስ/ እና ከአደገኛ አውሬ /የዱር እንስሳትን/ ለመከላከል እንደሚጠቅም መግለጽ። በተጨማሪም ተማሪዎቹን ትምህርት ቤታቸውንና በየአካባቢያቸው የሚገኙ ቤቶችን እንዲቃኙ /እንዲመለከቱ/ ማድረግ። ለቤቶቹ መስሪያ አገልግሎት ላይ የዋሉ ቁሳቁሶችን እንዲለዩ ማድረግ። ይህንንም በአካባቢ ከሚገኙ

ቁሳቁሶች የሚሰሩ የመጠለያ አይነቶችን የሚያሳይ ስእላዊ መግለጫ ሰርቶ ወይም ተማሪዎች የተለያዩ የቤት ሞደሎችን እንዲሰሩ በማድረግ ትምህርቱን ማጠቃለል ይኖርብዎታል።

የትምህርት መር É መሣሪያዎች

- ሞዴሎች
- ሥእሎች
- ፎቶግራፎች

ግምገማና ምዘና /ግምገማና ክትትል/

- የመጠለያን ጥቅም እንዲዘረዝሩ መጠየቅ።
- ተማሪዎች በትምህርት ቤታቸው ውስጥ ያሉትን ቤቶች ከምን ከምን እንደተሰሩ እንዲገልፁ የቡድን ሥራ መስጠትና መከታተል።

የመልመ É 1.3. መልሶች

ሀ. 1. መ
2. መ
3. ሐ
4. ሀ
5. መ

ለ. 6. እውነት
7. ሐሰት
8. እውነት

## 1.3. በተደጋጋሚ የሚያጠቁን በሽታዎች

የተመደበለት ክፍለ ጊዜ ብዛት 11

ዝርዝር አላማዎች

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ ፡-

- በአካባቢያቸው በተደጋጋሚ የሚከሰቱና የተለመዱ በሽታዎችን ይዘረዝራሉ።
- በአካባቢያቸው በተደጋጋሚ የሚከሰቱ በሽታዎችን ምልክቶች ይለያሉ።

- በአካባቢያቸው በተደጋጋሚ የሚከሰቱ በሽታዎችን መተላለፊያ መንገዶች ይለያሉ።

ዝርዝር ይዘት

- በተደጋጋሚ የሚከሰቱ በሽታዎች
    - ጉንፋን
    - ወባ
    - ወስፋት
    - ተቅማጥ

የማስተማር መማር ዘዴዎች

መምህር ተማሪዎች በየአካባቢያቸው በተደጋጋሚ በማጥቃት የሚታወቁ የተለመዱ በሽታዎች የሚባሉትን እንደ ጉንፋን፣ወስፋት፣ ወባና ተቅማጥ በመዘርዘር ተማሪዎቹ እንዲረዱት ማድረግ። እነዚህን በዝርዝር በመጻፍና ተማዎችን ከቤተሰቦቻቸው መካከል ወይም እራሳቸው በየትኛው በሽታ አይነት ተጠቅተው እንደሚያውቁ እንዲናገሩ ማድረግ ። በተጨማሪም ምን ጉዳት እንዳደረሰባቸውና የበሽታው ምልክት ምን አይነት እንደነበር እንዲናገሩ ማድረግ። በዚህም ሂደት ተማሪዎቹ በአካባቢያቸው በተደጋጋሚ የማህበረሰቡን አባላት የሚያጠቃው በሽታ የትኛው እንደሆነ እንዲለዩ ማድረግ።

ሀ. ጉንፋን

ዝርዝር አላማዎች

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፦

- ጉንፋን በተደጋጋሚ የሚያጠቃቸው በሽታ መሆኑን ይለያሉ።
- የጉንፋን በሽታ መተላለፊያ መንገዱን ይዘርዝራሉ።
- የጉንፋን በሽታ ምልክቶች ምን ምን እንደሆኑ ይዘረዝራሉ።

ዝርዝር ይዘት

- ጉንፋን መተላለፊያ መንገድ
- ምልክቶቹ

የማስተማር መማር ዘዴዎች

መምህር ተማዎች በተደጋጋሚ ከሚያጠቃቸው በሽታ መሀከል ጉንፋን እንደሆነ እንዲረዱና መተላለፊያ መንገዱንም በትንፋሽ ከሰው ወደ ሰው፣ ከአፍንጫና ከአፍ የሚወጣ ፈሳሽ እንዲሁም ጉንፋን ሊይዘን የሚችለው በመጥፎ ሽታ ፤ መጠጫዎችን በጋራ በመጠቀም እንደሚሆን መግለጽ ። እራሳቸውን ከዚህ በተደጋጋሚ ከሚያጠቃቸው በሽታ እንዲጠብቁ መንገር። ምልክቶቹም ትኩሳት /ራስ ምታት/፣ ሳልና ከአፍንጫ የሚወጣ ፈሳሽ እንደሆኑ መግለጽ።

የትምህርት መር É መሳሪያዎች

- ስእሎች /ከመማሪያ መጽሐፍ ሥእል 1.15 ን ይመልከቱ/
- የሞቱ እንስሳዎች ያሉበት፣ የሻሻ ቦታን እንደ መረ É በመጠቀም በምሳሌ መልክ ማቅረብ።

ግምገማና ምዘና /ግምገማና ክትትል/

- ጉንፋን የሚላለፍባቸውን መንገዶች እንዲዘረዝሩ መጠየቅ።
- የጉንፋን በሽታ ምልክቶች እንዲናገሩ የቃል ጥያቄ መጠየቅ።
- የጉንፋን በሽታ በእነሱና በቤተሰባቸው ላይ ያደረሰውን ጉዳት እንዲናገሩ መጠየቅ።

ለ/ የወባ በሽታ

ዝርዝር አላማዎች

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፡-

- የወባ በሽታ መተላለፊያ መንገዱን ይዘረዝራሉ።
- የወባ በሽታ የሚያስከትለውን ጉዳት ይገልፃሉ።
- የወባ በሽታ ምልክቶችን ይዘረዝራሉ።

ዝርዝር ይዘት

- መተላለፊያ መንገድ
- ምልክቶችና የሚያስከትለው ጉዳት

የማስተማር መማር ዘዴዎች

መምህር ተማሪዎች የወባ በሽታ በተደጋጋሚ የሚያጠቃ በሽታ መሆኑን እንዲለዩ በማድረግ በወባ በሽታ ተይዞ የሚያውቅ ከተማሪዎች መሀከል ለክፍል ጓደኞቹ በበሽታው ምን አይነት ምልክቶችን እንዳየና የደረሰበትን ጉዳት እንዲናገር ማድረግ ተማሪዎች የወባ በሽታን ምልክትና የሚያመጣውን ጉዳት ለይተው እንዲያውቁ ማድረግ ። በተጨማሪም የወባ በሽታ በወባ ትንኝ ንክሻ የሚመጣ በሽታ መሆኑንና የወባ ትንኞችም የመራቢያ ቦታቸውን /ረግረጋማና ኩሬያማ/ መሆኑን በመግለጽ አካባቢያቸውን ሁልጊዜ ከወባ ትንኝ ነፃ ማድረግ እንዳለባቸው፤ የበሽታውም ምልክቶች ትኩሳት፣ ማንቀጥቀጥ፣ የምግብ ፍላጐት መቀነስና የመሣሠሉት መሆናቸውንና ይህም ሲሆን አፋጣኝ የበሽታውን አይነት ለመለየትና ለመዳን ወደ ሀኪም ቤት መሄድ አስፈላጊ እንደሆነ ይንገሩዋቸው።

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- ስእሎች /ከመማሪያ መጽሐፍ ሥእል 1.16 ይመልከቱ/
- ፓስተሮች

ግምገማና ምዘና /ግምገማና ክትትል/

- የወባ በሽታ መተላለፊያ መንገዶቹን በቃል መጠየቅ።
- የወባ በሽታ ምልክቶችን ለይተው እንዲናገሩ መጠየቅ።

ሐ/ ተቅማጥ

ዝርዝር አላማዎች

ተማሪዎች ይህን ትምህረት ከተማሩ በኋላ ፡-

- የተቅማጥ በሽታ መንስኤዎችን ይገልፃሉ።

- የተቅማጥ በሽታ ምልክቶችን ይዘረዝራሉ።

ዝርዝር ይዘት

- መንስኤ
- ምልክት

የማስተማር መማር ዘዴዎች

መምህር የተቅማጥ በሽታ በጥቃቅን ሕዋሳት /በአይን በማይታይ/ የሚመጣ ከሰው ወደ ሰው የሚተላፍ መሆኑን መግለጽ ጠቀሜታው የጐላ ነው። አያይዘውም የተቅማጥ በሽታ መንስኤዎች የተበከለ ምግብ በመመገብ፣ የተበከለ ውሃ ወይም ንጽሕናው ያልተጠበቀ ውሃ በመጠጣት እንደሁም የግልና የአካባቢን ንጽሕና ባለመጠበቅ፣ ንጽሕናው ባልተጠበቀ የመመገቢያ እቃ በመጠቀምመሆኑን መግለጽ ተማሪዎቹ ከችግሮቹ እንዲጠነቀቁ ሊረዳቸው እንደሚችል መገንዘብ ያስፈልጋል።

በተቅማጥ በሽታ ተጠቅቶ የሚያውቅ ተማሪ ምልክቶቹን ለክፍል ጋደኞቹ እንዲናገር በማድረግ ተማሪዎች የተቅማጥ በሽታ ምልክቶችን እንዲለዩ ማድረግ ትምህርቱን ይበልጥ ተጨባጭ ለማድረግ ያግዝዎታል።

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- ስእሎች
- ፓስተሮች
- ፎቶግራፎች

ግምገማና ምዘና /ግምገማና ክትትል/

- የተቅማጥ በሽታ መንስኤዎችን እንዲዘረዝሩ መጠየቅ።
- የተቅማጥ በሽታ ምልክቶች ምን ምን እንደሆኑ የመልመጃ ጥየቄዎችን በመስጠት እንዲሰሩ መርዳት።

መ/ ወስፋት

ዝርዝር አላማዎች

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፡-

- የወስፋት በሽታ ምክንያቶች ምን ምን እንደሆኑ ይገልፃሉ።
- የወስፋት በሽታ መተላለፊያ መንገዶች ምን ምን እንደሆኑ ይዘረዝራሉ።

ዝርዝር ይዘት

- መተላለፊያ መንገድ
- ምልክቶቹ

የማስተማር መማር ዘዴዎች

መምህር በወስፋት በሽታ ተጠቅተው የሚያውቁ ተማሪዎችን በመጠየቅና የደረሰባቸውን ጉዳትና ችግር ለክፍል ተማሪዎች እንዲናገሩ ማድረግ ። በተጨማሪም ምን አይነት ምልክቶችን እንዳዩ እንዲናገሩ ማድረግ። ወስፋት የሚባለው በአንጀታችን ውስጥ የሚኖር ጥገኛ ትል ነው። ይህም ትል ከአንጀታችን ውስጥ ያለውን የተጣራ ምግብ በመሻማት እንደሚኖዳና ምልክቶቹ ማቅለሽለሽ፣ የምግብ ፍላጐት መቀነስና መክሳት፣ ወዘተ. መሆናቸውን በመዘርዘር ማስረዳት። የወባ በሽታ መተላለፊያ መንገዶች የተበከለ ውሃ በመጠጣትና የተበከለ ምግብ በመመገብ ሊመጣ እንደሚችል ለተማሪዎች መግለጽ።

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- ፓስተሮች
- ስእሎች /ከመማሪያ መጽሐፍ ስእል 1.18 ይመልከቱ/

ግምገማና ምዘና /ግምገማና ክትትል/

- የወስፋት በሽታ ምክንያቶች እንዲገልጹ መጠየቅ።
- የወስፋት በሽታ መተላለፊያ መንገዶች ምን ምን እንደሆኑ እንዲዘረዝሩ የቃል ጥያቄ መጠየቅ።
- የወስፋት በሽታ ምልክቶቹን እንዲዘረዝሩ መጠየቅ።

ኤድስ

ዝርዝር አላማዎች

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፦

- ኤድስ በሽታ የሚያመጣው ሕዋስ ምን ምን አይነት ጉዳት እንደሚያደርስ ይገልፃሉ።
- የኤድስ በሽታ መተላለፊያ መንገዱን ይዘረዝራሉ።
- የኤድስ በሽታ የማይተላለፍባቸውን መንገዶች ይተነትናሉ።

ዝርዝር ይዘት

ኤድስ /ኤች አይ.ቪ /

- የሚያስከትለው ጉዳት
- መተላለፊያ መንገዶቹ
- የማይተላለፍበት መንገዶች

የማስተማር መማር ዘዴዎች

መምህር ተማሪዎች ስለ ኤድስ ግንዘቤውና እውቀቱ ላይኖራቸው ስለሚችል በሽታው መድሃኒት የሌለው በበሽታው የተያዘ ሰው መዳን የማይችልና ገዳይ በሽታ መሆኑን መግለጽ ። የበሽታው አምጪ ሕዋስ ኤች አይ ቪ ኤድስ መሆኑንና ይህም ሕዋስ የሰውነት የመከላከል አቅምን በማዳከም ለሞት የሚዳርግና በሰው አካል ውስጥ በሽታን ለመከለከል የሚያስችለውን የአካል ክፍል ሃይል በማዳከምና በመጉዳት የሚያጠቃን በሽታ መሆኑን መግለጽ። የመተላለፊያ መንገዶችም ጥንቃቄ በጐደለው ወሊድ ማለትም ከእናት ወደ ልጅ በወሊድ ጊዜ /በባሕላዊ አዋላጅ ከተገላገለች እትብቱ ሲቆረጥ በሚደማበት ጊዜ በደም አማካይነት በንክኪ ሊተላለፍ እንደሚችል/፣ ሌላው በተጠቀመበት ጥፍር መቁረጫ በመጠቀም፣ ባልፀዱ የሕክምና መሳሪያዎች መገልገል፣ በጋራ የጥርስ ብሩሽ መጠቀም በሽታው መተላለፍ እንደሚችል መግለጽ። ከዚህ ጐን ለጐን የማይተላለፍባቸው መንገዶች አብሮ በመጫወት፣ አብሮ በመብላት፣ በወባ ትንኝ ንክሻ፣ ሰላምታ በመለዋወጥ በሽታው እንደማይተላለፍ በስእል በማስደገፍና ተማሪዎች በጨዋታ /በድራማ/ መልክ ተዘጋጅተው እንዲያቀርቡ ማድረግ ትምህርቱን ይበልጥ ተጨባጭ ያደርግልዎታል።

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- ስእሎች
- ፓስተሮች

ግምገማና ምዘና /ግምገማና ክትትል/

- ኤድስ በሽታ የሚያመጣውን ሕዋስ ምን እንደሆነ በቃል መጠየቅ።
- የኤች አይ ቪ ኤድስ በሽታ መተላለፊያ መንገዶችን እንዲዘረዝሩ መጠየቅ
- የኤች አይ ቪ በሽታ የማይተላለፍባቸውን መንገደች በመግለጽና የቤት ስራ በስጠት መከታተል።

በሽታን መከላከል

ዝርዝር አላማዎች

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፦

- በአካባቢያቸው የሚገኙ በተደጋጋሚ የሚያጠቃቸው ተላላፊ በሽታዎች እንዴት መከላከል እንደሚቻል ይገልፃሉ።
- በተደጋጋሚ የሚያጠቋቸውን በሽታዎች የእያንዳንዳቸውን የመከላከያ ዘዴ ይለያሉ።

ዝርዝር ይዘት

መከላከያ ዘዴ

- ጉንፋን
- የወባ በሽታ
- ተቅማጥ
- ወስፋት
- ኤድስ

የማስተማር መማር ዘዴዎች

መምህር ጉንፋን በምንተነፍሰው አየር ውስጥ በመሰራጨት እንደሚላለፍ ተምረዋል፤ ታዲያ የጉንፋን በሽታ እንዴት መከላከል እንችላለን?

መተንፈስ ማቆም አይቻልም ነገር ግን የየክፍሎቻችንን በሮችና መስኮቶች በመክፈት አየር እንደልብ እንዲገባና እንዲወጣ በማድረግ፤ የአየርን ንጽሕና በመጠበቅ እንደሁም በጉንፋን የተየዘ ሰው አፉንና አፍንጫውን በንፁህ ጨርቅ ወይም መሀረብ በመያዝ እንዲስል በመግለጽ የጉንፋን በሽታን መከላከል እንደሚቻል መንገር።

የተቅማጥ በሽታ የግልና የአካባቢን ንጽሕና ባለመጠበቅ እንደሚተላለፍ ተምረዋል። ይህም በሽታ መከላከል የሚቻለው ከተፀዳዳን በኋላ፣ ምግብ ከመመገባችን በፊትና በኋላ፣ በውሃና በሳሙና እጃችንን በመታጠብ፣ የመመገቢያና የመጠጫ እቃዎችን በንጽሕና በመያዝ የተቅማጥ በሽታን መከላከል እንደሚቻል መግለጽ።

የወባ ወሽታ የሚተላለፈው በወባ ትንኝ አማካይነት መሆኑን ተረድተዋል። ይህን በሽታ በአጐበር ውስጥ በመተኛትና በአካባቢያቸው የወባ ትንኝ የሚራባበትን የረጋ ውሃ ወይም ኩሬ እንዳይኖር በማድረግ መከላከል እንደሚቻል መግለጽ።

ወስፋት በሽታ መተላለፊያ መንገድ ንጽሕናው ያልተጠበቀ ውሃና ምግብ መጠቀም እንደሆነ ተምረዋል። ነገር ግን ይህን በሽታ ንጽሕናው  የተጠበቀ ውሃን፤ ምግብንና ሌሎችንም ነገሮች በመጠቀም መከላከል እንደሚቻል መግለጽ።

ኤድስ በደም ንክኪ ይተላለፋል። የኤድስ በሽታ እንዳይዘን ከሌላ ሰው ደም ጋር ከመነካካት መቆጠብ፣ በደም የተበከሉ ነገሮችን አለመንካት፣ የኤድስ በሽታን ለመከላከል እንደምንችል መግለጽና ትምህርቱን መቋጨት ።

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- ስእሎች
- ፓስተሮች

ግምገማና ምዘና /ግምገማና ክትትል/

- በተደጋጋሚ የሚያጠቁ በሽታዎች የመከላከያ ዘዴዎችን እንዲለዩ መጠየቅ።
- በተደጋጋሚ የሚያጠቁ የእያንዳንዳቸውን በሽታዎች በምን በምን አይነት ሁኔታ መከላከል እንደሚቻል የቤት ሥራ በመስጠት እንዲሰሩ ማድረግ።

የመልመ **É 1.4** መልሶች

ሀ. 1.ሐ

2.መ

3. ለ

ለ. 4. እውነት

5. ሐሰት

## **1.4.** አምስቱ የስሜት ሕዋሣት

የተመደበለት ክፍለ ጊዜ ብዛት 28

የስሜት ሕዋሳት ስም

ዝርዝር አላማዎች

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፡-

- አምስቱን የስሜት ሕዋሳት ስም ይናገራሉ።
- አምስቱን የስሜት ሕዋሳት ይለያሉ።

ዝርዝር ይዘት

- አይን
- አፍንጫ
- ጆሮ
- ምላስ
- ቆዳ

የማስተማር መማር ዘዴዎች፡-

መምህር ተማሪዎች የስሜት ሕዋሳት አይነቶችን እንዲዘረዝሩ መጀመሪያ መግለጽ። ቀጥሎም አንድ ተማሪ በማስነሳት አንድ የስሜት ሕዋስ እያመለከተ /በራሱ ሰውነት/ እንዲናገር ማድረግ። እንዲሁም በስእልና ሞዴሎችን በመጠቀም ተማሪዎች የስሜት ሕዋሶቻቸውን ማለትም አይናቸውን፣ ጆሮአቸውን፣ አፍንጫቸውን፣ ምላሳቸውንና ቆዳቸውን እንዲያሳዩ መጠየቅ።

መምህር በትምህርት ቤት ውስጥ አምስቱን የስሜት ሕዋሳት የሚያሳይ ስእል ወይም ሞዴል ከሌለ ከተማሪዎች ጋር በመሆን ስእሉን ማዘጋጀት። በተማሪው መማሪያ መጽሐፍ ላይ ያለውን ስእል /1.30 አምስቱ የስሜት ሕዋሳት/ የሚለውን በትምህርት መርጃ መሳሪያነት ይጠቀሙ።

የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

- ስእሎች
- ሞዴሎች

ግምገማና ምዘና /ግምገማና ክትትል/

- አምስቱን የስሜት ሕዋሳት ስሞች እንዲዘረዝሩ መጠየቅ።
- አምስቱን የስሜት ሕዋሳት አይነቶች የሰውነት ክፍሎቻቸው ላይ ያሉትን እያመለከቱ እንዲናገሩ መጠየቅ።

የስሜት ሕዋሳት ክፍሎች ተግባራት

ዝርዝር አላማዎች

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ ፦

- የስሜት ሕዋሳትን ጥቅም ይዘረዝራሉ።
- የስሜት ሕዋሳትን ጥቅሞች ይለያሉ።

ዝርዝር ይዘት

- ጥቅም
    - አይን ለማየት
    - ጆሮ ለመስማት
    - ምላስ ለመቅመስ
    - አፍንጫ ለማሽተት
    - ቆዳ ለመዳሰስ

የማስተማር መማር ዘዴዎች

መምህር ተማሪዎች የስሜት ሕዋሶቻቸውን እያመለከቱ ጥቅማቸውን እንዲናገሩ በማድረግ በጨዋታ መልክ ማስተማር።

ለምሳሌ ፦ አንድ ተማሪ ጆሮውን እያመለከተ የጆሮን ጥቅም በመናገር እና አይኑን እያመለከተ አይን ለማየት፣ ምላሱን እያመለከተ ለመቅመስ፣ አፍንጫውን እያመለከተ ለማሽተት፣ በእጁ እየዳሰሰ እጅ /ቆዳ/ ለመዳሰስ እንደሚጠቅም እንዲናገር በማድረግ ትምህርቱን መቋጨት ።

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- ስእሎች
- ሞዴሎች

ግምገማና ምዘና /ግምገማና ክትትል/

- የስሜት ሕዋሶቻቸውን እያሳዩ ጥቅማቸውን መጠየቅ።
- የስሜት ሕዋሶቻቸውን ጥቅም መልመ É በመስጠት እንደለዩ ማድረግ።

አይን

ዝርዝር አላማዎች

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፡-

- የማየት የስሜት ሕዋስን በመጠቀም የሚያዩትን ይናገራሉ።
- የብርሃን ምንጮችን ይለያሉ።
- ቀለማትን ይለያሉ።

ዝርዝር ይዘት

- አይን
- የብርሃን ምንጭን ማወቅ
- ቀለማትን መለየት

ማስተማር መማር ዘዴዎች

መምህር የተለያዩ ብርሃን የሚሰጡ ነገሮችን ለምሳሌ ፡- ባትሪ፣ ኩራዝ፣ ፋኖስ፣ የፀሐይ ብርሃን፣ ጨረቃ፣ አምፓል፣ የኤሌክትሪክ/ የመሳሰሉትን በአካልበማቅረብና በስእል በማሳየት /የመማሪያ መጽሐፍ ሥእል 1.32/ በመጠቀም የብርሃን ምንጮችን እንዲለዩ ማድረግ። በመቀጠልም የተለየዩ ቀለማትን ቁርጥራጭ ጨርቃጨርቆችን በማሰባሰብ ቀለማትን በማሳየትና ትምህርቱንም ለማስተማር በሚመች መልኩ የተሰባሰቡትነ የጨርቃጨርቅ ቁርጥራጮችን በትልቅ ካርቶን ላይ በስፒል በማያያዝ በትምህርት መርጃ መሳሪያነት መጠቀም ። በተጨማሪ ተማሪዎች እነዚህን የብርሃን ምንጩችንና የቀለማት አይነቶችን አንድ በአንድ እንዲለዩ ማድረግ።

መምህር በተማሪዎች መማሪያ መጽሐፍ ላይ በቀረበው ተግባራዊ ክንዋኔ መሠረት ከእጽዋት ቀለማትን እንዴት አድርገው እንደሚያዘጋጁ በማሳየት በቡድንም ቢሆን እንዲተገብሩ ማድረግ።

የትምህርት መርጃ መሣሪያ

- የፀሐይ ብርሃን
- ጨረቃ
- ፋኖስ
- ኩራዝ
- ሻማ
- ባትሪ
- የተለያዩ ቀማት  ያላቸው ቁርጥራጭ ጨርቆች
- ቅጠላቅጠል
- ውሃ
- ስካር፤ ወዘተ.

ግምገማና ምዘና /ግምገማና ክትትል/

- የብርሃን ምንጮችን እንዲለዩ መጠየቅ።
- የተለያዩ ቀለማት ያላቸውን ነገሮች በማቅረብ በየቀለማቸው እንዲመድቡ የቃል ጥያቄ ማቅረብ።
- ከተለያዩ ቅጠላቅጠልና አበቦች ቀለማትን እንዲሰሩ በቡድን መስጠት። የእያንዳንዱን የቡድን ሥራ መገምገም።

ጆሮ

ዝርዝር አላማዎች

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፡-

- ዋና ዋና ድምጾችን ምንጮች ይለያሉ።
- የመስማት የሰውነት ክፍልን በመጠቀም ድምጽን ይለየሉ።

ዝርዝር ይዘት

- ጆሮ
    - ዋና ዋና ድምጾችን መለየት
    - የዱር አራዊት
    - የቤት እንስሳት

- የተለያዩ የሙዚቃ መሳሪያዎች
- የመኪና፣ የአውሮኘላን
- የተለያዩ የሰዎች ድምጽ

የማስተማር መማር ዘዴዎች

መምህር ተማሪዎች የቤት እንስሳትን ድምጾች እንዲለዩና የእንስሳት ድምጾችን አስመስለው እንዲያሰሙ በመጠየቅ ትምህርት መጀመር።

በተጨማሪም የተለያዩ የእንስሳት ድምጾችን የያዘ ካሴት በመፈለግ ወይም በቴኘ በመቅዳት ወደ ክፍል አምጥተው ለተማሪዎች ቢያሰሙ ትምህርቱን በቀላሉ ከማስተላለፍ በተጨማሪ ተማሪዎች ትምህርቱን በፍላጐት እንዲከታተሉ ያደርጋል። በመቀጠልም የቤት እንስሳት እንደመለያየታቸው መጠን ድምጾቻቸው እንደሚለያዩ መግለጽ።

መምህር ተማሪዎችን ስለ ዱር እንስሳት ድምጾች ለማስተማር ሲጀምሩ ተማሪዎችን ስለ ዱር እንስሳት የሚያውቁትን እንዲናገሩ በመጠየቅ ትምህርቱን መጀመር። በቴኘ የተቀዳ የተለያዩ የዱር እንስሳት ድምዖችን በማሰማት የዱር እንስሳቶቹም ልዩ ልዩ ድምጾች እንደሚያሰሙ በመናገርና ከተማሪዎች ማህከል የዱር እንስሳትን ድምጽ አስመስለው ማሰማት የሚችሉ ካሉ እንዲያሰሙ በማድረግና በቡድን በማወያየት ትምህርቱን ማጠቃለል።

የሞተር ድምጾች የሚለውን ንዑስ ርእስ ከመጀመርዎ በፊት ተማሪዎች ልዩ ልዩ ድምጾች የሚያሰሙ ሰው ሰራሽ ሞተሮች መኖራቸውን ስለሚያውቁ እነዚህን የድምጽ ምንጭ የሆኑ ነገሮችን ምን ምን እንደሆኑ እንዲዘረዝሩ ማድረግ። ለምሳሌ ፦ መኪና ፣ ባቡር፣ ሞተር ሳይክል፣ አይሮኘላን፣ ወፍጮ የመሳሰሉት ሰው ሰራሽ ተንቀሳቃሽ ነገሮች የተለያዩ ድምጾችን እንደሚያሰሙ በመጥቀስ ተማሪዎችን እነዚህ ሞተሮች የሚያመነጩትን ድምጽ እንዲያሰሙ በማድረግ ትምህርቱን ማቋጨት።

መምህር የሙዚቃ መሳሪያ ድምጾችን ንዑስ ርእስ ከመጀመርዎ በፊት ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚገኙ የሙዚቃ መሳሪያዎች ምን ምን እንደሆኑ እንዲናገሩ በማድረግ ትምህርቱን መጀመር። በተጨማሪ የባሕላዊም ሆነ የዘመናዊ መሳሪያዎች የተለያዩ ድምጾች እንደሚያወጡ በመጠቆም ወደ ክፍል ለናሙናነት በማምጣትና መሳሪያውን በመነካካት ድምጽ እንዲያሰሙ ማበረታታት። በቴኘም በመጠቀም የተቀዳውን የመሳሪያ ድምጽ ተማሪዎች ከለዩ በኋላ፦ እነዚህን ድምጾች አስመስለው እንዲያሰሙ መጠየቅ። በመጨረሻም በተማሪው መማሪያ መጽሐፍ ላይ ያለውን ሥእል 1.37 እና በአካባቢያቸው በሚያገኙት ቁሳቁስ ለትምህርት መርጃ መሳሪያነት

በቡድን ተከፋፍለው እንደሰሩ ማድረግ ። እነዚህንም ተማሪዎች ሊመለከቱት በሚችሉበት ቦታ ላይ ማንጠልጠልና ተማዎቹን በማወያየት ትምህርቱን ከዳር ማድረስ ።

መምህር የሰዎችን ድምጽ ማስተማር ከመጀመርዎ በፊት ተማሪዎች ሰዎች ሲደሰቱ፣ ሲያዝኑ የሚያሰሟቸውን ድምጾች በክፍል ውስጥ እንዲያሰሙ ማድረግ። በመቀጠልም ሰዎች የሳቅ ፣ የለቅሶ፣ የቁጣና የልመና ድምጽ በተለያዩ ጊዜና ለተለያዩ አገልግሎት እንደሚያሰሙ በመጠቀም ትምህርቱን መቋጨት።

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- ሬደዩ
- ቴፕ
- ካሴት
- በአካባቢው የተለመዱ የሙዚቃ መሣሪያዎች ወይም የሙዚቃ መሣሪያዎች ስእሎች /ከመማሪያ መጽሐፍ ሥእል 1.37 እና 1.38 ይመልከቱ/
- የሰዎችን ሁኔታ የሚገልጹ፡- ለምሳሌ የሣቅ፣ የለቅሶ፣ ወዘተ።

ግምገማና ምዘና / ግምገማና ክትትል/

- በቴፕ የተቀዱ የተለያዩ ድምጾችን በማሰማት ተማሪዎች የእያንዳንዱን የድምጽ ምንጮች እንዲናገሩ የቃል ጥያቄ ማቅረብ።
- የዱር ወይም የቤት እንስሳትን ድምጾች አስመስለው እንዲያሰሙ በቃል መጠየቅ።
- የተለያዩ የሙዚቃ መሣሪያ ድምጾችን እንዲለዩ መጠየቅ።
- ሰዎች በተለያዩ ምክንያቶች የሚያወጧቸውን ድምጾች ለይተው እንዲያሰሙ በክፍል ውስጥ የቃል ጥያቄ ማቅረብ።
- የባሕላዊ ሙዚቃ መሣሪያዎች በአካባቢያቸው ከሚገኙ ቁሳቁስ እንዲሰሩ በማድረግ የእያንዳንዱን የቡድን ሥራ መገምገም።

ምላስ

ዝርዝር አላማዎች

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፡-

- የመቅመሻ የስሜት ሕዋስን ይለያሉ፣

- የሚታወቁ ነገሮችን ጣእም ይናገራሉ።
- የተለያዩ ጣእሞችን በመቅመስ የጣእማቸውን አይነት ያስረዳሉ።
- አንድን ነገር ከመቅመሳቸው በፊት በጤና ላይ ጉዳት የማያስከትል መሆኑን የረጋግጣሉ።

ዝርዝር ይዘት

- የነገሮችን ጣእም መለየት፣
- ኮምጣጣ ፤ መራራ፤ ጣፋጭና ጨዋማ ፣
- ጣእም ለመለየት የሚያስፈልግ ጥንቃቄ፣

የማስተማር መማር ዘዴዎች

መምህር ለተማሪዎች ምላስ የምግቦቻችንን ጣእም የምናውቅበት የስሜት ሕዋስ መሆኑን ማስረዳት። የተለያዩ የጣእም አይነቶችን ተማሪዎች እንዲናገሩ ማድረግ፤ ለምሳሌ ጣፋጭ፣ መራራ፣ ጨዋማና ኮምጣጣ ጣእም የተለያዩ ንጥረ ነገሮችን ለመለየት ያስችላል። ተማሪዎች የተለያዩ የምግብ አይነቶች ምን አይነት ጣእም እንዳላቸው እንዲናገሩ ማድረግ። የማያውቋቸውን ነገሮች በምላስ መቅመስ አደገኛ መሆኑን ተማሪዎች በጭውውት ወይም በድራማ መልክ እንዲሰሩት የጭውውቱም መቋጫ የማይታወቅ ነገር የቀመሰ ሰው መርዝ ሆኖበት አደጋ እንደደረሰበት የሚያሳይ ቢሆን ይመረጣል።

መምህር በመጨረሻም ተማሪዎች የተለያዩ ጣእም ያላቸውን ለምሳሌ ጨው፣ ስኳር፣ የቡና ድቄት፣ ሎሚ /ኮምጣጤ/ የመሳሰሉትን ወደ ክፍል በማምጣት በተግባር በመቅመስ ጣእምን እንዲለዩ በማድረግ ትምህርቱን መቋጨት።

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- ስካር
- ጨው
- የቡና ዱቄት
- ሎሚ
- ቃሪያ
- ስእሎች /የተለያዩ ጣእም ያላቸውን ነገሮች ስእል/

ግምገማና ምዘና /ግምገማና ክትትል/

- የመቅመሻ ስሜት ሕዋስን እንዲናገሩ መጠየቅ።

- የተለያዩ ነገሮች ጣእም እንዲለዩ የተለያዩ ጣእም ያላቸውን ነገሮች ወደ ክፍል በማምጣትና በመቅመስ ጣእሞቻቸውን እንዲናረሩ መጠየቅ።
- የሚቀመሱ ሆነው በጤና ላይ ጉዳት የሚያደርሱ የሚሏቸውን በክፍል ውስጥ እንዲናገሩ የቃል ጥያቄ ማቅረብ።

አፍንጫ

ዝርዝር አላማዎች

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፦

- የማሽተት የስሜት ሕዋስን ይለያሉ ።
- በማሽተት የሚለዩ ነገሮችን የመለየት ችሎታ ይኖራቸዋል።
- ሊሽተቱ የሚገቡና የማይገቡ ነገሮች መኖራቸውን ይለያሉ።

ዝርዝር ይዘት

- በማሽተት የተለያዩ ነገሮችን መለየት
    - መልካም ሽታ ያላቸው
        - ሽቶ
        - ሰነደል
        - እጣን
        - አበባ ፤ ወዘተ
    - መጠፎ ሽታ ያላቸው ፦
        - ንጽሕናው ያልተጠበቀ ሽንት ቤት
        - የሞተ እንስሳ
        - የጫማ ሽታ፤ ወዘተ.
- በማሽተት የአንድን ነገር ሽታ ለመለየት መደረግ የሚባው ጥንቃቄ

የማስተማር መማር ዘዴዎች

መምህር ለተማሪዎች አፍንጫ የማሽተት የስሜት ሕዋሳት ክፍል እንደሆነ ይንገሯቸው። ተማሪዎች በአፍንጫቸው የተለያዩ ነገሮችን በማሽተት መለየታቸውን፤ ከአሁን በፊት ያላቸውን

ልምድ ለማወቅ ያስችል ዘንድ ጥያቄዎችን መጠየቅ። ምሳሌዎችን በመስጠት ጥሩና መጥፎ የሆኑ ሽታዎችን ተማሪዎች እንዲያውቁ ወይም እንዲለዩ ማድረግ።

ድራማ ወይም ጭውውት በማዘጋጀት ተማሪዎች የሚያውቁትን ነገር በማሽተት አደጋ የሚያደርስ መሆኑን የሚያመለክት የፊት ገጽታ በማሳየት ጥሩና መጥፎ የሆኑ ሽታዎችን እንዲለዩ ማድረግ። ይህንንም ጭውውት ወይም ድራማ ለመስራት የሚያስፈልጉ ነገሮችን ለምሳሌ፦ ጥሩ ሽታ ያላቸውን አበባ፤ ሰንደል፤ ሽቶና የመሳሰሉትን ወደ ክፍል በማምጣት እና መጥፎ ሽታ ያላቸውን በመዘርዘር እንዲለዩ ማድረግ።

የትምህርት መር É መሳሪያዎች

- ሰንደል
- አበባ
- እጣን
- ሽንት ቤት
- ሽቶ
- ቆሻሻ ያለበትን አካባቢ በምሳሌ በማንሳት

ግምገማና ምዘና /ግምገማና ክትትል/

- የማሽተት የስሜት ሕዋሶቻቸውን እንዲናገሩ መጠየቅ።
- ልዩ ልዩ ነገሮችን በማሽተት በመልካም መአዛና በመጥፎ ሽታ ለይተው እንዲመደቡ የቡድን ሥራ ማሰራት።
- በማሽተት ያሉበትን አካባቢ መልካምነትና መጥፎነት እንዲገልፁ የመስክ ጉብኝት ማድረግ።
- መሽተት የሚገቡና መሽተት የማይገቡ ነገሮችን ለይተው እንዲናገሩ የቃል ጥያቄ ማቅረብ።

ቆዳ

ዝርዝር አላማዎች

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፦

- የመዳሰስ የስሜት ሕዋስ ምን እንደሆነ ይለያሉ።
- የተለያዩ ነገሮች ሻካራ፣ ለስላሳ፣ ሙቅና ቀዝቃዛ መሆናቸውን ይናገራሉ።

ዝርዝር ይዘት

ነገሮችን መዳሰስ

- ሻካራና ለስላሳ
- ቅዝቃዜና ሙቀት

የማስተማር መማር ዘዴዎች

መምህር ተማሪዎች የተለያዩ ነገሮችን ወደ ክፍል በማምጣትለስላሳና ሻካራ መሆናቸውን እንዲገልፁና በረዶ መቀዝቀዙን የተለያየ የሰውነት ክፍሎችን በስነካት /በረዶ በሌለበት ቦታ የቀዘቀዘ ውሃ በተለያየ የሰውነት ክፍሎቻቸውን መጠቀም ይቻላል/ የሞቀ ውሃ ውስጥ እ**É**ቸውን በማስገባት እንዲለዩ ማድረግ።

ለዚህም አገልግሎት የተጠቀምነው የስሜት ሕዋስ ቆዳችን መሆኑን ማስገንዘብ። እንዲሁም በጣም የቀዘቀዘና በጣም የሞቀ ነገር መንካት ቆዳችን ላይ አደጋ ሊያስከትል እንደሚችል በመግለጽ ትምህርቱን መቋጨት።

የትምህርት መር**É** መሳሪያዎች

- በረዶ /በጣም የቀዘቀዘ ውሃ/
- የሞቀ ውሃ
- አሸዋ
- ጥጥ

ግምገማና ምዘና /ግምገማና ክትትል/

- ለስላሳና ሻካራ ነገሮችን እንዲዘረዝሩ መጠየቅ።
- ቀዝቃዛና ሙቅ ነገሮችን በመንካት በማቅረብ እንደለዩ ማድረግ።

የመልመ**É 1.5** መልሶች

ሀ. 1. እውነት
2. እውነት
3. እውነት

ለ. 1. መ

2. ሐ

3. ሠ

4. ሀ

5. ለ

ሐ. 1.ሐ

2. ሀ

3. ሐ

የክለሳመልመጃ መልሶች

ሀ. 1. እውነት

2. ሐሰት

3. እውነት

ለ. 4. ለ

5. ሐ

6. ሀ

ሐ. 7. ሐ

8. ሐ

9. ሐ

10. ሀ

መ. 11. አብሮ በመመገብ

አብሮ በመጫወት

በወባ ትንኝ ንክሻ

ሰላምታ በመለዋወጥ /በመጨባበጥ/

12. ትከሻ፣ ጡንቻ፣ ክንድ፣ ጭን፣ ሆድ፣ ደረት፣ መዳፍ፣ የእጅ ጣት፣

ቁርጭምጭሚት ፣ ጉልበት፣ ቅልጥም፣ የእግር ጣት ናቸው።

# ክፍለ ትምህርት ሁለት

## 2. ቤተሰቦቻችን

የተመደበለት ክፍለ ጊዜ ብዛት 48

ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቅ ውጤት ፦ ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ ፦

- የቅርብ ቤተሰቦቻቸውን አባላትና በቤተሰብ ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎ ይገልፃሉ።
- የምግብ ምንጭ የሆኑትን አዝዕርት፤ የእርሻ ቦታን ያመለክታሉ፣ የእህል ዘሮችን ስም በመለየት፣ ለምን አይነት ምግብነት እንደማውሉና እንዴት አድርገው ከብልሽት እንደሚጠብቋቸው ይናገራሉ።
- የተለያዩ አልባሳትና መጠለያ በመጥራት ከምን ከምን እንደሚሰሩ ያስረዳሉ።
- የተለያዩ የቤት ውስጥ መገልገያዎችንና ዕቃዎችን ስም ይናገራሉ፤ ጥቅማቸውንም ይዘረዝራሉ፤ ከምን እንደተሰሩና እንዴት መጠቀምና መጠበቅ እንደማገባም ያሰረዳሉ።
- ሳይንሳዊ የሆነ ክህሎትን በማስተዋል፤ በመጠየቅ፤ ከሌሎች ጋር ግንኙነት በመፍጠርና በመተጋገዝ ያዳብራሉ።

### **2.1.** የቤተሰብ አባላት

የተመደበለት ክፍለ ጊዜ ብዛት 11

ዝርዝር አላማዎች

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ ፦

- የቤተሰብን አባላት ይዘረዝራሉ።
- የቤተሰብ አባላት ዝምድናን ይለያሉ።
- የጾታን ልዩነት ያስረዳሉ።

ዝርዝር ይዘት

### **2.1.** የቤተሰብ አባላት

የቤተሰብ አባላት ዝርዝር

አክብሮት ለታላላቆቻችን

የማስተማር መማር ዘዴዎች

መምህር የቤተሰብ አባላት የምንላቸውን አያቶች፣ ወላጆች፣ ወንድሞች፣ እህቶች አጎቶችና አክስቶች ብቻ እነደሆኑ ተማሪዎች እንዲረዱና እንዲለዩ በማድረግ ተማሪዎች ስለቤተሰብ አባላቶቻቸው ለሌሎች ክፍል ጓደኞቻቸው እንዲናገሩ እድል ይስጧቸው። በተጨማሪም ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የቤተሰብ አባላትን የሚያሣይ ድራማ እነዲሰሩ ካደረጉ በኋላ ስለ ቤተሰብ አባላት የዝምድና ትስስር ገለፃ በመስጠት ትምህርቱን ማዳበር ይጠበቅብዎታል።

ተማሪዎችን ስለ ጾታ መሰረታዊ እውቀት እንዲጨብጡ በማድረግ ጾታ በተፈጥሮ እንደሚገኝ እንዲሁም በተፈጥሮ ሁለት አይነት የጾታ አይነቶች እንዳሉ በመግለፅ፤ ማንም ሰው በእናቱ ማህፀን ውስጥ ሴት ወይም ወንድ ሊሆኑ እንደማችሉ ማስረዳት ያስፈልጋል። ከዚያም ተማሪዎቹ የቤተሰብ አባሎቻቸውን /አባት፤ እናት፤ ወንድምና እህት / በጾታቸው እንዲመድቡዋቸው እድል በመስጠት ጾታ ተፈጥሮአዊ መሆኑን በውይይትና በገለፃ ማዳበር ትምህርቱን ይበልጥ ተጨባጭ ለማድረግ ያግዝዎታል።

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- ስዕሎች /አባት፣ እናት፣ ልጆችን የሚያሳይ ሥዕል ከመማሪያ መጽሐፍ ሥዕል 2.1. ይመልከቱ/
- ፎቶግራፎች
- ሞዴሎች

ግምገማና ምዘና /ግምገማና ክትትል/

- የቤተሰብ አባላትን እንዲዘረዝሩ መጠየቅ ።
- የቤተሰብ አባላትን የዝምድና ትስስር እንዲገልፁ መጠየቅ።
- የጾታን ልዩነት በስዕሎች እንዲለዩ መጠየቅ።

የአኗኗር ሁኔታ

ዝርዝር አላማዎች

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ ፦

- የቤተሰብን አባላት በቤተሰብ ውስጥ ያላቸውን የሥራ ድርሻ ይናገራሉ።
- ወንድና ሴት በማህበራዊ ኑሮ እኩል የሥራ ድርሻ እንዳላቸው ይለያሉ።

ዝርዝር ይዘት

የአኗኗር ሁኔታ

ለመኖር የቤተሰብ አባላት ምን ያደርጋሉ?

የማስተማር መማር ዘዴዎች

መምህር የቤተሰብ አባላት ከቤት ውጪ ያላቸውን ተጨማሪ የሥራ ድርሻ ግብርና፣ ንግድ፣ ውትድርና፣ ሙያተኛ፣ የቢሮ ስራና የቀን ስራ በማለት መመደብና መግለፅ ይቻላል። በተጨማሪ ተራ በተራ በማስነሳትና ቤተሰቦቻቸውን በየትኛው የሥራ መስክ እንደሚመደቡ መጠየቅና መመዝገብ፤ በመጨረሻም በየትኛው የሥራ መስክ ላይ የብዙ ተማሪዎች ቤተሰቦች እንደተሳተፉና የትኛው የሥራ መስክ በአካባቢው ብዙ ሰው እንዳሳተፈ ማስረዳት ተማሪዎች የተለያዩ የሥራ መስኮች የሚያስፈልጉ እንቅስቃሴዎችን /ሁኔታዎችን/ እያስመሰሉ በድራማ ወይም በጭውውት እንዲያሳዩ ማበረታታትና መደገፍ ያስፈልጋል።

የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

- ስዕሎች
- ፖስተሮች

ግምገማና ምዘና /ግምገማና ክትትል/

- የቤተሰብ አባላት ያላቸውን የሥራ ድርሻ ምን ምን እነደሆነ መጠየቅ።

- በተለያዩ የሥራ መስኮች እንቅስቃሴ ተማሪዎች በድራማ መልክ ሲጫወቱ መከታተል።

የወላጆች የሥሪ ድርሻ

ዝርዝር ዓላማዎች

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፦

- የወላጆችን የሥራ ድርሻ ኃላፊነት ያብራራሉ።
- የቤተሰባቸውን የገቢ ምንጭ ምን እንደሆነ ይዘረዝራሉ።
- ከገቢ ምንጭ የመቆጠብ ጠቀሜታን ያስረዳሉ።

ዝርዝር ይዘት

- መልካም አርአያነት
- መልካም አስተዳደር
- እንክብካቤና ፍቅር
- የገቢምንጭ መፍጠርና ማስተዳደር

የማስተማር መማር ዘዴዎች

መምህር ተማሪዎች ስለ ወላጆቻቸው የስራ ድርሻና ኃላፊነት ግንዛቤ ሊኖራቸው ስለሚችል ቀለል ባሉ ጥያቄዎች ትምህርቱን መጀመር ተማሪዎች እንዲሳተፉ ያግዛል። ተማሪዎች ከሚሰጧቸው መልሶች በመነሳት ስለ መልካም አርአያነት፣ ስለ መልካም አስተዳደር፣ ስለ እንክብካቤና ፍቅር በውይይት መልክ ገለፃ መስጠት አስፈላጊ ነው። ውይይቱን በማስፋፋት ከወላጆች የሥራ ድርሻ መሀል መልካም አርአያነትን፣ መልካም አስተዳደርንና እንዲሁም እንክብካቤና ፍቅር መሆናቸውን ማስረዳት ይኖርብዎታል።

በተጨማሪ እነዚህን የሥሪ ድርሻዎች በቤተሰቦቻቸው ውስጥ ማን እንደሚተገብራቸው በጥያቄ መልክ አንስቶ ምላሽ እንዲሰጡ ማድረግ ጠቀሜታው የጎላ ነው።

ከወላጆች ኃላፊነት መካከል የገቢ ምንጭ መፍጠር፣ በገቢ ማስተዳደርና ቆጥቦ ንብረትን ማፍራት ይህንንም ኃላፊነት ከወላጆቻቸው ወይም ከቤተሰቦቻቸው መሀከል ማን እየተወጣ እንደሆነ በመጠየቅ የተማሪዎቹን ግንዛቤ ማስፋት አስፈላጊ ይሆናል።

ስለዚህ የቤተሰባቸው የገቢ ምንጭ /ንግድ፣እርሻ ፣የመንግሥት ሥራ ፣ የቀን ስራ ወዘተ./ እንደሚሆን ማብራሪያ መስጠት ይኖርብዎታል። ከሚገኘውም ገቢ ቆጥቦ ንብረትን ማፍራት እንደሚቻል ገለፃ በማድረግና ትምህርቱን በመከለስ መቋጨት።

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- የወላጆች የስራ ድርሻ የሚያሳይ ስዕል /ከመማሪያ መፅሐፍ ሥዕል 2.5 ን ይምልከቱ/

ግምገማና ምዘና /ግምገማና ክትትል/

- የወላጆችን የሥሪ ድርሻ ለይተው እንዲናገሩ መጠየቅ።
- የወላጆችን ኃላፊነት እንዲዘረዝሩየቤት ሥራ መስጠት፡
- የቤተሰቦቻቸውን የገቢ ምንጮች እንዲናገሩ መጠየቅ።

የልጆች የሥራ ድርሻ

ዝርዝር ዓላማዎች

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፡-

- ልጆች በቤተሰብ ውስጥ ያላቸውን የሥሪ ድርሻ ይለያሉ።
- የቤተሰብን ደንብ ማክበርና ለቤተሰብ መታዘዝን ይለማመዳሉ።

ዝርዝር ይዘት

- መማር
- የቤተሰብን ደንብ ማክበር
- መታዘዝ
- ቤተሰብን በአቅም መርዳት

የመማር ማስተማር ዘዴዎች

መምህር ተማሪዎች በቤተሰብ ውስጥ ያላቸውን የሥራ ድርሻ በመጠየቅ ትምህርቱን መጀመር ። በመቀጠልም በሚኖሩበት ቤተሰብ ውስጥ ደንብ መኖሩንና አለመኖሩን በመጠየቅ ደንቡ ካለ ልጆች እንዴት አድርገው እንደሚያከብሩ መጠየቅ ፤ ካላቸው ደንብም ውስጥ ዋና ዋና የሚሉትን ለክፍልጓደኞቻቸው እንዲነግሯቸው ማበረታታት። ተማሪዎችን ስለመማር፣ የቤተሰብን ደንብ ስለማክበር፣ ስለመታዘዝና ቤተሰብን በአቅም ስለመርዳት ጠቀሜታማብራራትና መግለፅ ።

ይህም አካባቢያቸውን ለማወቅ ወደፊትም ጥሩ ሥራ በመስራት ሀገራቸውንና ወገናቸውን ለመርዳት እንደሚጠቅም መግለፅ። ቤተሰብን በአቅም መረዳት ጥሩ እነደሆነና የሥሪ ክቡርነትን አያይዞ ማስገንዘብ።

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- ስዕሎች /ከመማሪያ መጽሐፍ ሥዕል 2.8 ን ይመልከቱ/

ግምገማና ምዘና /ግምገማና ክትትል/

- ልጆች በቤተሰብ ውስጥ ያላቸውን የሥሪ ድርሻ ለይተው እንዲናገሩ መጠየቅ።
- የቤተሰብን ደንብ ማክበርና መታዘዝን በጥያቄ መገምገም።
- ለቤተሰብ የሚያሳዩትን ዋና ዋና መልካም ባሕሪ ለይተው እነዲናገሩ መጠየቅ።

የቤተሰብ መልካም ገንኙነት

ዝርዝር ዓላማዎች

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፦

- የቤተሰብ መልካም ግንኙነት ምን ምን እንሆነ ይለያሉ።
- የሌሎችን ቤተሰብ እንዴት መርዳትና ማክበር እንደሚገባ ይገልፃሉ።
- መልካም ግንኙነትን በተግባር ያሳያሉ።

ዝርዝር ይዘት

ቤተሰባዊ መልካም ግንኙነት

- መተሳሰብ
- መግባባት
- መፈቃቀር
- መከባበር
- በሥራ መረዳዳት
- ችግርን በጋራ መፍታትና

- ታማኝነት

የማስተማር መማር ዘዴዎች

መምህር የቤተሰብ መልካም ግንኙነት ምንነት ተማሪዎች ገለፃ እንዲያደርጉ በማድረግና እነዚህን መልካም ግንኙነት በመለየትና የመልካም ግንኙነት ጠቀሜታ ምን እንደሆነ እንዲያውቁ በተረት ወይም በጭውውትና በድራማ መልክ ልምምድ እንዲያደርጉ ማድረግ። ቤተሰብ መልካም ግንኙነት ከሚያስፈልጋቸው የሕብረተሰብ ክፍል እንደሆነ በመግለፅ የቤተሰባዊ መልካም ግንኙነት ከሚባሉት ጥቂቶቹ መግባባት፣መተሳሰብ፣ መፈቃቀር፣ መረዳዳት ፣መከባበር ፣ ችግርን በጋራ መፍታትና ታማኝነት መሆናቸውን በማብራራትና በማስገንዘብ ሴቶችንና ወንዶችን በማህበራዊ ኑሮ ውሰጥ ያላቸውን ሚናና እኩልነት በጭውውት መልክ እንዲያሳዩ በማድረግ በመጨረሻ ስለቤተሰብ አባላት የሥራ ድርሻና መልካም ግንኙነት ክለሳ በማድረግ ትምህርቱን ማጠቃለል የተሻለ እንደሚሆን ይታመናል።

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- ፎቶግራፍ
- ስዕሎች

ግምገማና ምዘና /ግምገማና ክትትል/

- የቤተሰብ መልካም ግንኙነት ምን ምን እንደሆነ እነዲለዩ መጠየቅ።
- በድራማ መልክ ቤተሰባዊ መልካም ግንኙነት ሲለማመዱ መከታተል።

የመልመጃ **2.1.** መልሶች

ሀ. 1. እውነት

2. ሐሰት

3. እውነት

ለ. 4. መ

5. ሀ

6. ለ

7. ሐ

ሐ. 8. ሀ

9. ሐ

10. ለ

## 2.2. የቤተሰብ መሰረታዊ ፍላጎቶች

የተመደበለት ክፍለ ጊዜ ብዛት 17

ም ግ ብ

ዝርዝር ዓላማዎች

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ ፦

- ግብርና የምግብ ዋስትና ማረጋገጫ መሆኑን ይለያሉ።
- በቤታቸው ውስጥ የእህል ዘሮችንና ከእህል ዘሮች የሚዘጋጁ ምግቦችን ይዘረዝራሉ።
- ለምግብነት የሚውልና የማይውሉ እፅዋትን ይለያሉ።

ዝርዝር ይዘት

ምግብ

- የምግብ ምንጭ
- የተለመዱ እህሎች
- የእህል ውጤቶች

የማስተማር መማር ዘዴዎች

መምህር ግብርና ዋናው የገቢ ምንጭ መሆኑን ተማሪዎች እንዲረዱትና እንዲለዩት ማድረግ። ተማሪዎችን በአካባቢያቸው የሚበቅሉና ለምግብነት የሚውሉትን የማያውቋቸውን የእህል ዓይነቶች እነዲናገሩ መጠየቅ። በተጨማሪም በአካባቢያቸው የእህል ዘሮች በየትኛው ወቅት ምርት እንደሚሰበሰብ መናገር እንዲሞክሩ ማድረግ መልካም ነው።

ከተማሪዎቹም ከሚገኘው መልስ አዝዕርት የሚሰበሰቡበትን የቀን መቁጠሪያ መስራት ያስችላል። ይህም እንደየአካባቢያቸው ከሚያውቋቸው አዝዕርት መካከል መማሪያ መጽሐፍ ላይ ሰንጠረዥ 2.1. ያለውን በመጠቀም እንዲሰሩ ማድረግ ይኖርብዎታል።

የሚበቅሉ ነገር ግን ለምግብነት የማይውሉ የዕፅዋት አይነቶች ለይተው እንዲናገሩ መጠየቅ። ለምሳሌ ፡- ዛፍ የሚተከለው ጥላን እና እንጨትን ለማግኘት ነው። ቀርከሃ ለሽመና ሥራና ለቤት ውሰጥ መገልገያ እንደሚውል በመግለፅ ትምህርቱን መቋጨት።

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- በአካባቢ የሚገኙ የእህል አይነቶች
- ለምግብነት ከማይውሉ እፅዋት የሚሰሩ ቁሳቁሶች

ግምገማና ምዘና /ግምገማና ክትትል/

- የምግብ ምንጭ ምን እንደሆነ መጠየቅ።
- በየአካባቢያቸው የሚገኙትን የእህል አይነቶች እነዲዘረዝሩ መጠየቅ።
- የተለመዱ የምግብ አይነቶች እንዲዘረዝሩየቃል ጥያቄ መጠየቅ።
- ለምግብነት ከማይውሉ እፅዋት የሚሰሩ ነገሮችን እንዲዘረዝሩ መጠየቅ።

ልብስ

ዝርዝር ዓላማዎች

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፡-

- በየአካባቢያቸው የተለያዩ የልብስ አይነቶች እንዳሉ ይለያሉ።
- በአካባቢያቸው ልብስ ለመስራት የሚያስፈልጉ ነገሮችን ስም ይዘረዝራሉ።
- በቤተሰባቸው ውስጥ የሚለበሱ ልብሶች ከምን ከምን እንደተሰሩ ይለያሉ።

ዝርዝር ይዘት

- ልብስ
- የልብስ ዓይነት
- ልብስ ለመስራት የሚያስፈልጉ ነገሮች

የማስተማር ማመር ዘዴዎች

መምህር ተማሪዎች የተለዩ ልብስ አይነቶችን እንዲዘረዝሩ መጠየቅና መመዝገብ፤ ከሚዘረዝሩት ውስጥ ቡልኮ፣ ቁምጣ ፣ ቀሚስ ፣ ኮት ፣ጃኬት ፣ ሱሪ ፣ሹራብ፣ ብርድ ልብስ ፣ ኩታ፣ ጋቢ ፣ ሸሚዝ እንደሆኑ መግለፅ።

ተማሪዎች በክረምት ብቻ የሚለበሱና በበጋ የሚለበሱ በማለት ልብሶችን እንዲከፋፍሉና እንዲገነዘቡ ማድረግ። በተጨማሪ ከምን ከምን ግብአቶች /ጥሬ ዕቃዎች/ እንደሚሰሩ እንዲዘረዝሩ በማድረግ የሚዘረዝሩአቸውንም ግብአቶች /ጥሬ ዕቃዎች/ መዝግበው እንዲያሳዩ ማድረግ አስፈላጊ ይሆናል። ከተመዘገቡትም ዝርዝሮች ውሰጥ ጥጥ፣ ሱፍ፣ቆዳና ናይለን መሆናቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። እንዲሁም ተማሪዎች በቡድን በቡድንበመከፋፈል ጫማና ጋቢ ከምን እንደሚሰሩ እንዲወያዩና እንዲለዩ በማድረግ ትምህርቱን በክለሳ መጨረስ የተሻለ አማራጭ ይሆናል።

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

-የተለያዩ የልብስ አይነቶችን /ተማሪዎቹ በለበሱት አይነት ልብስ/

- ጥጥ

- ኮቆዳ የተሰሩ / ልብስ፣ ጫማ ፣ ቦርሣ፣ ቀበቶ/

- ቁርጥራጭ ጨርቆች /ከናይለን ፣ ከሱፍ፣ ከጥጥና ከቆዳ የተሰሩ ልብሶች ቁርጥራጭ/

ግምገማና ምዘና /ግምገማና ክትትል/

- በቤተሰባቸው ውስጥ ተዘውትረው የሚለበሱ ልብሶችን እንዲዘረዝሩ መጠየቅ።
- ልብስ ከምን ከምን እንደሚሰራ የቃል ጥያቄ መጠየቅ።
- በክረምትና በበጋ የሚለበሱ ልበሶች ምን ዓይነት እነደሆኑ መ

መ ጠ ለ ያ

ዝርዝር አላማዎች

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ ፡-

- በአካባቢያቸው የተለያዩ መጠለያ መኖራቸውን ይለያሉ።
- በአካባቢያቸው ለመጠለያ ሥራ የሚውሉ የተለያዩ የዕቃ አይነቶችን ስም ይዘረዝራሉ፤ ያሳያሉ።

ዝርዝር ይዘት

መጠለያ

የመጠለያ አይነቶች

- የቆርቆሮ ቤት
- የሳር ቤት
- አፓርትማ ቤቶች

ለመጠለያ ሥራ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች

- ጭቃ
- ሳር
- ድንጋይ
- ቆርቆሮ፣ ወዘተ

የማስተማር መማር ዘዴዎች

መምህር መጠለያ የምንላቸው ጎጆ ቤት፣ አፓርትማና የቆርቆሮ ቤቶች ናቸው። ለመጠለያ ሥሪ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች ጭቃ ፣ ሳር፣ ድንጋይ፣ ብሎኬት ፣ እንጨት፣ ብረት፣ ቆርቆሮ ፣ ሸክላና፣ አልሙኒየም ናቸው።

ተማሪዎችን በትምህርትቤት ግቢና ውጪ በመውሰድ ለመጠለያ መስሪያ ሊውሉ የሚችሉ የተለያዩ ቁሳቁሶች እንዲለዩና እንዲመዘግቡ ማድረግ። ወደ ክፍል በሚመለሱበት ጊዜ ለመጠለያ ሥራ የዋሉ ቁሳቁሶች ዝርዝር ይዘው እንዲመጡና በቡድን ለሌሎች የክፍል ተማሪዎች እንዲያስተዋውቁ ማድረግ ። ተማሪዎችን ለመጠለያ ሥራ የሚውሉ ነገሮችን ለምን ሥራ እንደምንጠቀምበት መጠየቅ። ለምሳሌ ፡- ጭቃን ለግድግዳ ሥራ ስንጠቀምበት፤ ሳርን ግን ለጣራ ስራ እንጠቀምበታለን ። ለምን እንደነዚህ አንደምናደርግ እንዲናገሩ በመጠየቅ በመማሪያ መጽሐፍ ላይ ያለውን ስዕል 2.11 አሳድጎ በመሳል በስዕሎች የተደገፈ ተጨማሪ ገለፃ በማድረግ ትምህርቱን መቋጨት።

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- የተለዩ የቤት አይነቶችን የሚያሳዩ ስዕሎች
- ፎቶግራፎች
- የተለያዩ የመጠለያ መስሪያ ቁሳቁሶች /ቆርቆሮ፣ ጭቃ፣ ሳር...../

ግምገማና ምዘና /ግምገማና ክትትል/

- ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚገኙ ቤቶች ከምን ከምን እንደተሰሩ እንዲናገሩ የቃል ጥያቄዎችን ማቅረብ።
- ተማሪዎች በቡድን ሆነው የመጠለያ ሞዴሎችን እንዲሰሩ እድል በመስጠት መገምገም /ሞዴሎችን በካርቶን፣ በእንጨት ፣ በጭቃ ሊሰሩ ይችላሉ/።

የመልመጃ **2.2.** መልሶች

ሀ. 1. እውነት

2. እውነት

3. ሐሰት

4. ሐሰት

5. እውነት

ለ. 6. ሐ

7. ሀ

8. ሐ

9. ለ

10. ሐ

## **2.3.** የቤት ቁሳቁሶች

የተመደበለት ክፍል ጊዜ ብዛት 20 የቤት

ቁሳቁሶች ዓይነት

ዝርዝር ዓላማዎች

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ ፦

- የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁሶችን ይዘረዝራሉ።

- የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁሶችን ዓይነት ይለያሉ።

ዝርዝር ይዘት

የቤት ቁሳቁስ አይነት

- የኤሌክትሪክ ዕቃዎች
- የተለያዩ የቤት ውስጥ መገልግያ ዕቃዎች

የማስተማር መማር ዘዴዎች

መምህር ተማሪዎች በቤታቸው ውስጥ የሚገኙትን የተለያዩ ዕቃዎች ለምሳሌ ፡- የቤት ውሰጥ መገልገያ ስለሆኑ የኤሌክትሪክ መሣሪዎች እንዲሁም ስለተለያዩ የቤት ውስጠ መገልገያ ዕቃዎች እንዲናገሩ ማድረግ ተማሪዎቹ ይበልጥ እንዲረዱ ያግዝዎታል።

መምህር የቤት ውስጥ መገልገያዎችን በተለይም የተለመዱ የኤሌክትሪክ መሣሪያዎች ለምሳሌ ፡- የኤሌክትሪክ የእንጀራ ምጣድ፣ የወጥ ማብሰያ የኤሌክትሪክ ምድጃ፣ እንዲሁም ሌሎች የቤት ውስጥ ዕቃዎችን ጠረጴዛ፣ ወንበር፣ አልጋ፣ ቴሌቪዥን ፣ ሬዲዮና የመሳሰሉትን በመጥራትና በማሳየት ትምህርቱን ማጠቃለል ይቻላል።

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- ስዕሎች / የተለያዩ የቤት ውስጥ ዕቃዎች ከመማሪያ መጽሐፍ 2.12፣ 2.13 ፣ 2.14፣ 2.15፣ 2.16 ና 2.17 ን ይመልከቱ/
- ሞዴሎች
- እውን መረጃዎች

ግምገማና ምዘና /ግምገማና ክትትል/

- የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁሶችን እንዲዘረዝሩ የቃል ጥያቄ መጠየቅ።
- የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁሶችን በአይነታቸው እንዲለዩ መጠየቅ።

- በቡድን ሆነው ከቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎችን በአካባቢያቸው ከሚያገኟቸው ቁሳቁስ ሞዴሎችን እነዲሰሩ ማድረግና መከታተል።

የቤት ቁሳቁስ አገልግሎተ

ዝርዝር ዓላማዎች

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ ፦

- የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁሶችን አገልግሎት ይለያሉ።
- የቤትውስጥ ቁሳቁሶችን የማዕድ /የመመገቢያ/፣ የመታኛና የመቀመጫ ብለው በመለየት ይመድባሉ።
- ቀላል የቤት ውስጥ መሳሪያዎችን ይለያሉ።
- ስለታመና ሹል ቁሳቁሶችን በጥንቃቄ ይጠቀማሉ።

ዝርዝር ይዘት

- የቤት ቁሳቁሶች አገልግሎት
  - ለምግብና ለመጠጥ ማዘጋጃ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶ
  - ለመመገቢያና ለመጠጫ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች
  - ለመቀመጫና ለመኝታ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች
  - በቤት ውሰጥ ቀላል ሥራ ለመስራት የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች
  - ለመዝናኛና ለማስታወቂያ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች
- በቤት ውስጥ የሚደረጉ ጥንቃቄዎች

የማስተማር መማር ዘዴዎች

መምህር ተማሪዎችን የቤት ውስጥ ዕቃዎችን እንዴት ሊገለገሉባቸው እንደሚችሉ መጠየቅ። የቤት ውስጥ የተለያዩ ዕቃዎች ተፈጥሮአቸው የተለያየ ቢሆንም ከዚህ በታች የሚከተሉትን ማየት በቂ ይሆናል።

- ምግብ ለመመገብ የሚያገለግሉ /ትሪ፣ ቢላዋ፣ ሹካ፣ ማንኪያ፣ ሰሀን የመሳሰሉትን/

- ለሥራ የሚያገለግሉ / መዶሻ፣ መቀስ ፣ መጥረቢያ፣ መኮትኮቻ፣ አካፋ፣ ማጭድ፣ ዶማና የመሳሰሉት /
- ለመቀመጫ ለመተኛ የሚያገለግሉ / ወንበር፣ አልጋ፣ ጠረጴዛ፣ በርጩማ፣ የመሳሰሉት/
- ለመዝናኛና ማስታወቂያ የሚያገለግሉ / ቴሌቪዥን፣ ሬዲዮ የመሳሰሉት/ ናቸው።

እነዚህን የተለያዩ መገልገያ ዕቃዎችን ሥዕሎችንና ሞዴሎችን በመስራትና በመጠቀም አገልግሎታቸውን መግለፅ ።

መምህር ይህንን ንኡስ ርዕስ ከማጠቃለልዎ በፊት ተማሪዎች ከቤት ውስጥ ቁሳቁሶች መሀከል ስለታምና ሹል የሆኑትን ብቻ ለይተው እንዲዘረዝሩና እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው እነዲያስረዱ በመጠየቅ አስፈላጊውን ማብራሪያ እንዲሰጧቸው ይጠበቃል።

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- ሞዴሎች
- ስለዕሎች
- የተለያዩ ቁሳቁስ አይነት

ግልምገማና ምዘና / ግምገማና ክትትል/

- የተለያዩ የቤት ቁሳቁሶችን አገልግሎት እንዲዘረዝሩ መጠየቅ ።
- የተለያዩ የቁሳቁሶች ስዕል በማሳየት ስማቸውንና ጥቅማቸውን መጠየቅ።

የቤት ውስጥ መገልገያዎችን መስሪያ

ዝርዝር ዓላማዎች

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፡-

- የቤት ውስጥ ዕቃዎችን ለመስራት የሚያገለግሉ ነገሮችን ይዘረዝራሉ።
- የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎች የሚሰሩበትን ቁሳቁሶች ይለያሉ።

ዝርዝር ይዘት

- የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎችን መስሪያ

- ከእንጨት
- ከብረት
- ከፕላስቲክ
- ከሸክላ አፈር

የማስተማር መማር ዘዴዎች

መምህር የመገልገያ ዕቃዎቹ የተሰሩበትን ለይተው እንዲናገሩ ማድረግ። ለምሳሌ ፦ ከእንጨት የተሰሩ የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎች አንደ ጠረጴዛ ፣ ወንበር፣ አልጋ ወዘተ. ሲሆኑ ከብረት ሊሰሩ የሚችሉ የቤት ውሰጥ መገልገያ ዕቃዎች ሳህን ፣ ትሪ ፣ ብረትድስት፣ ጭልፋ፣ ማንኪያ፣ ሹካና የመሳሰሉት ናቸው። በሸክላ አፈር የሚሰሩ የቤት ውስጥ ዕቃዎች ሸክላ ድስት፣ ጀበና፣ የእንጀራ ምጣድ፣ የከሰል ማንደጃና የመሳሰሉት እንደሆኑ ለተማሪዎች በመግለፅ ትምህርቱን መቋጨት።

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- ከሸክላ የተሰሩ ዕቃዎች /ድስት፣ ምጣድ፣ ጌጣጌጥ የመሳሰሉት /
- ከብረት የተሰሩ ዕቃዎች / ሹካ፣ ማንኪያ፣ ማንቆርቆሪያ፣ ጭልፋ የመሳሰሉት/
- ከእንጨት የተሰሩ ዕቃዎች / ጠረጴዛ፣ ወንበር የመሳሰሉት/
- ሞዴሎች
- ስዕሎች

ግምገማና ምዘና /ግምገማና ክትትል/

- የተለያዩ ለቤት ቁሳቁስ መሥሪያ የሚውሉ ነገሮችን እንዲዘረዝሩ መጠየቅ።
- በቡድን በመከፋፈል ከሸክላ አፈር የሚሰሩ የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁሶችን ሞዴል እንዲሰሩ ክትትል ማድረግ።

የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎች አያያዝ

ዝርዝር ዓላማዎች

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ ፦

- የቤት ውስጥ ዕቃዎችን እንዴት እንደሚቀመጡና እንዴት እንደሚይዙ ይናገራሉ።
- ለቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁሶች ማድረግ የሚገባቸውን ጥንቃቄዎች ያሳያሉ።
- በቤት ውስጥ የሚፈጠሩ አደጋዎችን እንዴት ማቃለል እንደሚቻል ይገልፃሉ።

ዝርዝር ይዘት

- የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎች አያያዝ
    - ንፅሕና
    - ጥንቃቄ

የማስተማር መማር ዘዴዎች

መምህር ተማሪዎች ተገቢ የሆነ የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎችን አጠቃቀም እንዲናገሩ ማድረግ። የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁሶችን ከተጠቀሙ በኋላ በየቦታው መጣል እንደማያስፈልግ ለተማሪዎቹ መናገር  ሲቆሽሹ ማጠብና መጥረግ ጠርሙስና ሸክላ የሆኑ የቤትውስጥ ዕቃዎች ተሰባሪዎች በመሆናቸው የተለየ አያያዝና ጥንቃቄ እንደሚያስፈልጋቸው መግለፅ።

የኤሌትሪክ መገልገያ ዕቃዎች እርጥበት ባለው እጅ መንካት አደገኛ ነው። ከተጠቀሙ በኋላ አድርቆና ጠርጎ ገመዶቹ ሰዎችን ጠልፈው እንዳይጥሉ ጠቅልሎ ማስቀመጥ እንደሚገባ ለተማሪዎች ማስገንዘብ።

ተማሪዎች ከቤት ውስጥ ዕቃዎች ጋር በተያያዘ የደረሰባቸው ችግር ካለ እንዲናገሩ መጠየቅና የደረሰውንም ችግር በምን ዓይነት መንገድ እንደተቃለለ ለሌሎች  ተማሪዎች እንዲናገሩ ማድረግ። በመጨረሻም ተማሪዎች የተለያዩ የቤት ውስጥ መገልገያዎችን እንዴት መያዝ እንዳለባቸው የቤት ስራ በመስጠት፣ በቤታቸው እንዴት አድርገው የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁሶችን እንደሚይዙ ከሞከሩ በኋላ፣ የሙከራ ውጤታቸውን ሪፖርት በማድረግ ትምህርቱን ማጠቃለል የተሻለ ይሆናል።

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- ስዕሎች /በመማሪያ መጽሐፍ ሥዕል 2.20 እና 2.21 ይመልከቱ/
- ሞዴሎች

ግምገማና ምዘና /ግምገማና ክትትል/

- የቤት ውስጥ ዕቃዎችን እንዴት እንደሚጠቀሙና እንዴት እንደሚይዙ እንዲናገሩ መጠየቅ።
- ለቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁሶች መደረግ የሚገባቸው ጥንቃቄዎች ምን ምን እንደሆነ የቤት ሥራ በመስጠትና እቤታቸው ተግብረውት እንዲመጡ ክትትል ማድረግ።
- በቤት ውሰጥ የሚፈጠሩ አደጋዎችን እንዴት ማቃለልና ጥንቃቄ መውሰድ እንደሚገባቸው የቃል ጥያቄ መጠየቅ።

## የመልመጃ **2.3.** መልሶች

ሀ. 1. እውነት

2. እውነት

3. ሐሰት

4. እውነት

5. ሐሰት

6. ሐሰት

ለ. 7. ሀ

8. ለ

9. ሐ

10. ለ

## የክለሳ ጥያቄዎች መልስ

ሀ. 1. ሀሰት

2. ሐሰት

3. እውነት

4. እውነት

5. እውነት

ለ. 6. ሰ

7. መ

8. ሀ

9. ለ

10. ሐ

ሐ. 1. ኩባያ፣ ብርጭቆ፣ ስኒ

2. እንክብካቤና ፍቅር፣ ጥሩ አስተዳደር፣ መልካም አርአያነት

3. ወንበር፣ ጠረጴዛ፣ አልጋ፣ ምጣድ፣ ፣ብረትድስት፣ ጀበና፣ ፣ሹካ፣ ማንኪያ፣ ሣህን፣ ስኒ፣ ኩባያ፣ ወዘተ.

## ክፍለ ትምህርት ሦስት

### 3. ትምህርት ቤታችን

የተመደበለት ክፍለ ጊዜ ብዛት 48

የክፍለ ትምህርቱ አጠቃላይ አላማዎች

- የትምህርት ቤታቸውን አካባቢና በትምህርት ቤታቸው የሚደረጉ ተግባራትን ይገልፃሉ።
- የወጡ ሕጎችንና ደንቦችን በትምህርት ቤት፣ በቤታቸውና በጎረቤታቸው እንዴት መፈፀም እንደሚገባቸው ያሳያሉ።
- ጥሩ ፀባይን በትምህርት ቤት፣ በቤታቸውና በጎረቤታቸው ያሳያሉ።
- በመንገድ ላይ የሚፈጠሩ አደጋዎችን እንዴት መከላከል እንደሚችሉ ይገልፃሉ።

- የተለያዩ እቃዎችን በንፋስ የሚንቀሳቀሱ የወረቀት ተሽከርካሪዎችን ይሰራሉ።
- ሳይንሳዊ የሆነ ክህሎት ያዳብራሉ፣ ማስተዋልን፣ መጠየቅ፣ መወያየት፣ ምስል መስራትና አብሮ በመስራት ያሳያሉ።

### **3.1.** የትምህርት ቤትችን ግቢ

የትምህርት ቤት ግቢ የያዛቸው ቦታዎች

የተመደበለት ክፍለ ጊዜ ብዛት 12

ዝርዝር አላማዎች

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ከተማሩ በኋላ ፡-

- የትምህርት ቤታቸውን ግቢ ሁኔታ ያስረዳሉ።
- የትምህርት ቤታቸውን አቅጣጫ ከቤታቸው በየትኛው አቅጣጫ እንደሚገኝ ይለያሉ።

ዝርዝር ይዘት

- የትምህርት ቤት ግቢ የያዘው ልዩ ልዩ ቦታዎች
    - ሽንት ቤት
    - ቤተ መጻሕፍ
    - መማሪያ ክፍሎች

የማስተማር መማር ዘዴዎች

መምህር! ተማሪዎች በትምህርት ቤታቸው አካባቢ የሚገኙ ዋና ዋና ነገሮችን እንዲዘረዝሩ መጠየቅ። ተማሪዎችን ያልጠቀሱዋቸውን ነገሮች ካሉ በማሟላት የትምህርት ቤታቸውን አቅጣጫን መግለጽ። የትምህርት ቤት መገኛ ለመናገር ተማሪዎች የግድ አራቱን አቅጣጫዎች ማለትም ምስራቅ ምእራብ ደቡብ እና ሰሜን አቅጣጫን ማወቅስላለባቸው የተለመደውን የአቅጣጫ አፈላለግ ዘዴን ማስተዋወቅ። ዘዴውም ፊታችንን ወደ ፀሐይ መውጫ መልሠን በመቆምና ሁለቱን ግራና ቀኝ እጆቻችንን በመዘርጋት በመቀጠልም ፊት ለፊተችን የፀሐይ መውጫ ምስራቅ እንደሚባል የፀሐይ መግቢያ አቅጣጫ ደግሞ ምእራብ እንደሚባል የግራ እጆችን አቅጣጫ ሰሜን እና የቀኝ እጃችን አቅጣጫ ደቡብ እንደሚባል መግለጽ።

ተማሪዎች በትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ እንዲዘዋወሩና በግቢው ውስጥ የሚገኙ ሕንፃዎችና የተለያዩ ነገሮችን በስዕል እንዲየስቀምጡ ማድረግ። እዚህ ላይ አስፈላጊ የሚሆነው በግቢ ውስጥ የተለያዩ ነገሮች የሚገኙበትን ቦታ  ለማመልከት በወረቀት ላይ በትንሽ መጠን እንዲያስቀምጡ መንገር ይኖርቦታል። የሚማሩበት ክፍል የት እንደሚገኝ በስዕሉ ላይ እንዲያሳዩ ማድረግ ።

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- ስእሎች
- ሞዴል /ከአንጨት ወይምከአካባቢ ቁሳቁስ የተሰሩ ምስራቅ ደቡብ ምእራብና ሰሜን አቅጣጫን የሚያሳይ ሞዴል/

ግምገማና ምዘና /ግምገማና ክትትል/

- ትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ ያሉ ቦታዎችን ዘርዝረው እንዲናገሩ መጠየቅ።
- ትምህርት ቤታቸው ከቤታቸው በየትኛው አቅጣጫ እንደሚገኝ መጠየቅ።

በትምህርት ቤት የሚናወኑ ተግባራት

ዝርዝር አላማዎች

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ ፡-

- በትምህርት ቤት ስለሚከናወኑ ተግባራት ይገልፃሉ።
- በትምህርት ቤት ውስጥ ማድረግ የሚባቸውን ነገሮች ይለያሉ።

ዝርዝር ይዘት

- መማር
- ማስተማር
- ልዩ ልዩ ስፖርታዊ ጨዋታዎች
- በክበባት መሳተፍ

የማስተማር መማር ዘዴዎች

መምህር በትምህርት ቤት የሚናወኑ እንቅስቃሴዎች ለመማር ማስተማር ሂደት ጠቃሚእንዲሆኑ በቅድሚያ መግለጽ። ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ የሚከናወኑ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን እንዲገልፁ ማድረግ። በትምህርት ቤት ውስጥ ምን ምን አይነት እንቅስቃሴዎች ቢኖሩ ጥሩ ነው? የሚሉትን በተጨማሪ እንዲገልጹ ማድረግ ለምሳሌ ፦ የስፓርት ቡድን የተለያዩ ክበባት ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች እንዳሉና ተማሪዎችም በእነዚህ እንቅስቃሴዎች እንዲሳተፉ ማድረግ።

የተዘረዘሩትን እንቅስቃሴዎች መመዝገብ በትምህርት ቤት ሊያዩዋቸው የሚፈልጉዋቸው እንቅስቃሴዎች ካሉ ተማሪዎችን በድጋሚ መጠየቅ።

የተለያዩ ቀለል ያሉ የሕብረት ጨዋታዎችን እንዲጫወቱ ማበረታታት ትምህርቱን ይበልጥ ተጨባጭ ለማድረግ ያግዝዎታል።

የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

- ለእንቅስቃሴዎች የሚያስፈልጉ ቁሳቁስ /ኳስ መረብ የተለያዩ ትምህርት ሰጪ የሆኑትን ለማስተላለፍ የሚረዱ ቴፕ፣ ድምጽ ማጉያ፣ ሬዲዮ፣ ወዘተ/ ።

ግምገማና ምዘና /ግምገማና ክትትል/

- በትምህርት ቤት ውስጥ የሚካሄድ ልዩ ልዩ እንቅስቃሴዎች ምን ምን እንደሆኑ መጠየቅ።
- በትምህርት ቤት ውስጥ በሚካሄዱ ተግባራት መሳተፋቸውን መተግበራቸውን መከታተልና መገምገም።

የመልመጃ **3.1.** መልሶች

ሀ. 1. እውነት

2. ሐሰት

3. ሐሰት

ለ. 4. ሀ

5. ሀ

6. ሐ

በትምህርት ቤት ውሰጥ የተማሪዎችመልካም ግንኙነት

ዝርዝር አላማዎች

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፡-

- ከማን ጋር እንደሚጫወቱ ምን እንደሚጫወቱ እና እንዴት እንደሚጫወቱ ይገልፃሉ።
- ከጓደኞቻቸው ጋር በምን አይነት ሁኔታ እንደሚግባቡ ይለያሉ።

ዝርዝር ይዘት

- መልካም ግንኙነት
    - መደማመጥ
    - መግባባት

የማስተማር መማር ዘዴዎች

መምህር ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ማህበረሰብ ጋር እንዴትና በምን ሁኔታ መግባባት እንዳለባቸው መግለጽ። ይህም ሲባል መደማመጥ ከሌለ መግባባት እንደማይኖርና አንዱ የሌላውን ማዳመጥ አስፈላጊ እንደሆነ መናገር ይኖርብዎታል።

በትምህርት ቤት ውስጥ ለመምህሮቻቸው ለትምህርት ቤት ሰራተኞችና ለጓደኞቻቸው አክብሮት ማሳየት እንዳለባቸው በመግለጽ ትምህርቱን መቋጨት እንዳለብዎት መዘንጋት የለብዎትም።

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- ሥዕሎች /ከመማሪያ መጽሐፍ ሥእል 3.6 እና 3.7 ን ይመልከቱ።

ግምገማና ምዘና /ግምገማና ክትትል/

ተማሪዎች እርስ በእርሳቸው እንዴት እንደሚግባቡ መጠየቅ።
ከትምህርት ቤት ማህበረሰብ ጋር በምን አይነት ሁኔታ እንደሚግባቡ መጠየቅ።

## **3.2.** የትምህርት ቤት ሕግና መመሪያ ማክበር

የተመደበለት ክፍለ ጊዜ ብዛት 8

የትምህርት ቤት መመሪያ

ዝርዝር አላማዎች

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፡-

- የትምህርት ቤት ደንብና ሥርአትን ይለያሉ።
- የትምህርት ቤትን ሕግ እንዴት እንደሚያከብሩ ይናገራሉ።

ዝርዝር ይዘት

የትምህርት ቤት መመሪያ

- ደንብና መመሪያ

የማስተማር መማር ዘዴዎች

መምህር ተማሪዎች የትምህርት ቤት ደንብና ሥርአት ምን ማለት እንደሆነና በውሰጡም የሚያካትታቸውን ነገሮች እንዲናገሩ በማድረግ ትምህርቱን መጀመር የተሻለ ይሆናል። ተማሪዎችም ያልዘረዘሯቸውን ጉዳዮች ካሉ በመጨመር ትምህርቱን ማብራራት። እነዚህን ደንቦችና ሥርአቶች እንዴት አድርገው በክፍል ውስጥና ከክፍል ውጪ፣ በትምህርት ክፍል ጊዜ፣ በእረፍት ሰአትና በጨዋታ ጊዜ ሊያከብሩ እንደሚገባቸው በዝርዝር ማስረዳት ጠቀሜታው ከፍ ያለ ነው።

በቤታቸው ውስጥ ስላሉ ሕጐችና ደንቦች እንዲናገሩ በማበረታታት እነዚህም ሊያጠቃልሉ የሚችሉት ወላጆቻቸውንና ታላላቆቻቸውን ማክበር፣ በጠዋት ከመኝታቸው ተነስተው የትምህርት መሣሪያዎቻቸውን በማዘጋጀት፣ የቤት ሥራቸውን ማታ ማታ በመስራት እንደሆነ በመግለጽ ትምህርቱን መቋጨት ያስፈልጋል።

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- ስእሎች /ከመማሪያ መጽሐፍ ሥእል 3.8 እና 3.9 ን ይመልከቱ/።

ግምገማና ምዘና /ግምገማና ክትትል/

- በቡድን ሆነው በእረፍታቸውና በጨዋታ ጊዜ ማድረግ ስለሚገባቸው ሥነ ሥርአቶችና ጥንቃቄዎችን እንዲገልፁ መጠየቅ።

- ጊዜያቸውን በአግባቡ እንዴት እንደሚጠቀሙ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንደናገሩ መጠየቅ።

## የመልመጃ 3.2 መልሶች

ሀ. 1. እውነት

2. እውነት

3. ሐሰት

ለ. 4. ሐ

5. ሐ

## 3.3. ጥሩ /መልካም/ የሆነ የግል ግንኙነት

የተመደበለት ክፍለ ጊዜ ብዛት 6

በቤትና በጐረቤት ያለ መልካም ግንኙነት

ዝርዝር አላማዎች

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ከተማሩ በኋላ ፦

- ጥሩ የሆነ ሥነ ምግባርን ለበተሰቦቻቸውና ለጐረቤቶቻቸው ያሳያሉ።
- ከቤተሰቦቻቸውና ከጐረቤቶቻቸው እንዴት መልካም ግንኙነት ሊኖራቸው እንደሚገባ ይለያሉ።

ዝርዝር ይዘት

- በቤት ውስጥ ያለ መልካም ግንኙነት
- ከጎረቤት ጋር ያለ መልካም ግንኙነት

የማስተማር መማር ዘዴዎች

ተማሪዎች ጥሩ የሆነ ምግባርን የሚያሳዩ ሁኔታዎችን በድራማ መልክ እንዲያቀርቡ በማበረታታት ማገዝና መደገፍ ይኖርቦታል። ይኸውም ሰላምታ አሰጣጥን፣ ግልጽነትን፣ ቀናነትን፣

ተባባሪነትና እርዳታ ሰጪነትን የሚያካትት እንዲሆን መርዳት። ከዚህ ክንውን በኋላ በድራማው በቀረቡ ሁኔታዎች ላይ የክፍል ተማሪዎች ውይይት እንዲያደርጉ የማድረግ ጠቀሜታው ከፍ ያለ ነው። በተጨማሪም የመልካም ጉርብትና ባሕሪያት የሆኑትን ማለትም በጋራ መስራትና መረዳዳት መከባበር፣ በጾታና በሃይማኖት እኩልነት ማመን፣ አብሮ ችግርንእና ደስታን መካፈል እና የታመመን መጠየቅ የመሳሰሉት መሆናቸውን በዝርዝር ማስረዳትና ትምህርቱን መቋጨት ይጠበቅብዎታል።

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- ስእሎች /ከመማሪያ መጽሐፍ ሥእል 3.11 እና 3.12 ን ይመልከቱ።/
- ፎቶግራፎች

ግምገማና ምዘና /ግምገማና ክትትል/

- በቤታቸውና በጎረቤቶቻቸው የሚያሳዩትን ሥነ ምግባሮች ምን ምን እንደሆኑ መጠየቅ።

የመልመጃ **3.3.** መልሶች

ሀ. 1 እውነት

2. እውነት

3. ሐሰት

ለ. 4. ሀ

5. ሐ

## **3.4.** የመንገድ ላይ ጥንቃቄ

የተመደበለት ክፍለ ጊዜ ብዛት 12

የመንገድ ላይ አደጋዎች

ዝርዝር አላማዎች

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፦

- የመንገድ ላይ አደጋዎችን መንስኤ ይገልፃሉ።
- የመኪና መንገድ እንዴት ማቋረጥ እንደሚገባቸው ይለያሉ።

ዝርዝር ይዘት

- የመንገድ ላይ አደጋዎች
- ጥንቃቄዎች

የማስተማር መማር ዘዴዎች

መምህር ተማሪዎች በመንገድ ላይ በሚከሰቱ አደጋዎች ለይ እንዲወያዩ ማድረግ። ይኸውም ግራና ቀኝ ሳይመለከቱ መንገድ ማቋረጥ ከተፈቀደው የእግር መንገድ ውጪ መሄድ፣ ተገቢ ያልሆነ የብስክሌት አነዳድ፣ በመኪና መንገድ ለይ እንስሳትን መንዳት፣ መንገድ ዘግቶ ተያይዞ መጓዝ፣ በመኪና መንገድ ላይ መጫወትና ሌሎችም እንደሆኑ ለተማሪዎች መግለጽና ማስረዳት።

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- ስእሎች
- ፓስተሮች
- የተለያዩ የመኪና መንገድ ላይ ምልክቶች

ግምገማና ምዘና /ግምገማና ክትትል/

- የመንገድ ላይ አደጋዎችን የሚያመጡ የጥንቃቄ ጉድለቶችን ለይተው እንዲዘረዝሩ መጠየቅ።
- የመኪና መንገድን እንዴት ማቋረት እንደሚገባቸው መጠየቅ።

የመንገድ ላይ አደጋዎችን መከለከል

ዝርዝር አላማዎች

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፡-

- የመንገድ ላይ አደጋዎችን እንዴት መከላከል እንደሚቻል ይገልፃሉ።
- በጥንቃቄ መንገድ ማቋረጥ እንደሚገባ ጥንቃቄዎችንም ይዘረዝራሉ፤ ለሌሎችም ምክር ይለግሳሉ።

ዝርዝር ይዘት

የመንግድ ላይ አደጋ መከላከያ ጥንቃቄዎች

- ሌሎችን መርዳት /ሕፃናትን፤ አካል ጉዳተኞችንና አዛውንቶችን/

## የማስተማር መማር ዘዴዎች

መምህር ተማሪዎች በመንገድ ላይ የሚከሰቱ አደጋዎችን ለመቀነስ በሚያስችሉ ሁኔታዎች ላይ ውይይት እንዲያደርጉ ማበረታታት። ውይይቱ የሚያካትተው፡-

- በመኪና መንገድ ላይ ንቃት ባለው ሁኔታ መጓዝ፣
- መንገድ በማቋረጥ ላይ እያሉ አደጋ ለሚያደርሱ ነገሮች ጥንቃቄ እንዲያደርጉ መንገር፣
- ድልድዮችን፣ መረማመጃዎችንና የሚያዳልጡ ቦታዎችን በጥንቃቄ እንዲያልፉ መግለጽ፣
- በመንገድ ላይና በመንገድ ዳር አለመጫወት፣
- የመንገድ ማቋረጫ መስመሮችን በጥንቃቄና በአግባቡ መጠቀም እንዲችሉ ማስረዳት የሚሉትን ነጥቦች ይሆናል።

ተማሪዎች ያላቸውን ልምድ እንዲያካፍሉ ማድረግ ውጤቱም ምን ያህል አስከፊ እንደሆነ እንዲገነዘቡ በመጫወቻ ቦታቸው አካባቢ እንዲሁም በመንገድ ላይ ሊጠበቁ የሚገባቸውን ጥንቃቄዎች በተግባር እንዲያሳዩ ማድረግ ተማሪዎች በመታጠፊያ መንገዶች ላይ በጥንቃቄ ማለፍ ፣ግራና ቀኝ መመልከት፣ በመንገዱ ግልፅና ተሸከርካሪ የሌለ ከሆነ በቀጥታ መስመር በመሄድ ማለትም /በዜብራ/ ማቋረጥና የመሳሰሉትን እንዲያሳዩ በማድረግ ትምህርቱን መቋጨት ያስፈልጋል።

## የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- ስዕሎች
- ፖስተሮች
- ፎቶግራፎች
- የተለያዩ የትራፊክ ምልክቶች

## ግምገማና ምዘና /ግምገማና ክትትል/

- የመንገድ ላይ አደጋዎች እንዴት መከላከል እንደሚችሉ የቃል ጥያቄ መጠየቅ።

- የመኪና መንገድ ሲያቋርጡ መውሰድ የሚገባቸውን ጥንቃቄ በድራማ መልክ ሲያቀርቡ መከታተልና መገምገም።

የመልመጃ **3.4** መልሶች

ሀ. 1. እውነት

2. ሐሰት

ለ. 3. ሐ

4. ሐ

5. ለ

**3.5.** በትምህርት ቤታችን የምናደርጋቸው እንቅስቃሴዎች

የተመደበለት ክፍለ ጊዜ ብዛት 10

ወረቀት በመጠቀም የተለያዩ ቅርፃ ቅርጾችን መስራት

ዝርዝር ዓላማዎች

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፦

- በወረቀት በመጠቀም ሳጥኖችንና በነፋስ የሚሽከረከሩ ሽክርክሪት መጫወቻዎችን በመስራት ያሳያሉ።
- የተለያዩ ነገሮችን በወረቀትና በሌሎች ቁሳቁሶች መስራት እንደሚችሉ ይረዳሉ።

ዝርዝር ይዘት

- ወረቀት በመጠቀም የተለያዩ ቅረፃ ቅርጾችን መስራት
  - መጫወቻዎችን
  - ሳጥኖችን
  - በንፋስ የሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪ መጫዎቻዎችን

የማስተማር መማር ዘዴዎች

መምህር ተማሪዎች በቅድሚያ የሚሰሯቸውን ነገሮች በወረቀት ላይ በስዕል በእንዲያሠፍሩ በማድረግ እንዲሁም ቅደም ተከተላቸውን በትክክል እንዲጠብቁ መንገር። አስፈላጊ የሆኑ

ቀለማትን፣ ማጣበቂያዎችን፣ መቁረጫዎችን በማዘጋጀት ቅርፃ ቅርጾችን እንዲሰሩ በማድረግ እና ትምህርቱን መቋጨት።

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- ወረቀት
- እርሳስ
- ማስመሪያ
- መቀስ
- ማጣበቂያ

ግምገማና ምዘና /ግምገማና ክትትል/

- ተማሪዎች በተለያዩ ነገሮችን በወረቀት እንዲሰሩ ማድረግና መከታተል።

የክለሳ ጥያቄዎችመልሶች

ሀ. 1. እውነት
2. እውነት
3. ሐሰት
4. ሐሰት
5. ሐሰት

ለ. 6. ለ
7. ሐ
8. መ
9. ሀ

ሐ. 10. ለ
11. ሐ
12. ሐ

# ክፍለ ትምህርት አራት

**4.** መንደራችን ቀበሌያችን

የተመደበለት ክፍለ ጊዜ 57

የክፍለ ትምህርቱ አጠቃላይ አላማዎች

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ከተማሩ በኋላ ፡-

- የትምህርት ቤታቸውን፣ የቤታቸውንና የቀበሌያቸውን መገኛ ያመለክታሉ።
- የውሃን፣ የአየርንና የአፈርን ጥቅም ይናገራሉ፤ አፈር /ጭቃ/ በመጠቀም የተለያዩ ቅርፃቅርጾችን ይሰራሉ።
- እጽዋትን፣ ትንንሽ እጽዋትና ዛፎችን በማለት መመደብ ይችላሉ፤ እንዴት አድርገው እንደሚንከባከቡ ይገልፃሉ።
- እንስሳትን ለማዳና የዱር በማለት ይመድባሉ፤ የሚሰጡትን ጥቅምና እንዴት መጠበቅ እንደሚገባ ይናገራሉ።
- ስራዎችንና ሙያዎችንየመንግሥትና መንግሥተዊ ያልሆኑ በማለት ይመድባሉ።
- የሥራን ክቡርነትና ጥቅም ይናገራሉ። ለተለያዩ ስራዎችም ያላቸውን ፍቅር ይገልፃሉ።
- የመጓጓዣ ጥቅምንና አይነት ባሕላዊና ዘመናዊ የመጓጓዣ አይነቶችን ምሳሌ በመስጠት ይገልፃሉ።
- ሳይንሳዊ የሆነ የምርምር ክህሎት ያዳብራሉ። ምልከተ፣ መጠየቅ፣ ግንኙነት፤ አብሮ የመስራት ልምድ ያዳብራሉ። ነገሮችን በመልክ በመልካቸው ይመድባሉ።

**4.1.** የቀበሌያችን መገኛ

የተመደበለተ ክፍለ ጊዜ ብዛት 9

ዝርዝር አላማዎች

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፦

- ቀኝ ፣ ግራ፣ ፊት ለፊትና ጀርባን ይለያሉ።
- የትምህርት ቤታቸውን፣ የቤታቸውንና የቀበሌያቸውን መገኛ /አቅጣጫ/ ያመለክታሉ።

ዝርዝር ይዘት

አቅጣጫ መናገር

የመኖሪያ ቤት፣ የትምህርት ቤትና የቀበሌ አቅጣጫ

የማስተማር መማር ዘዴዎች

መምህር! ተማሪዎች በየአካባቢያቸው ያሉ ነገሮች የሚገኙበት የተለያዩ ነገሮች መገኛ አቅጣጫ ግራ፣ ቀኝ፣ ፊት ለፊትና የኋላ በማለት እንዲናገሩ ማድረግ። ተማሪዎች በጨዋታ መልክ ከፊት፣ ከኋላ፣ ከቀኝና ከግራ በመቆም እነዚህን አቅጣጫዎች እንዲለዩ ማድረግ። በተጨማሪ አካባቢያቸውን በማየት በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ የሚገኙትን ሕንፃዎች፣ ዛፎች፣ ሽንት ቤቶች አቅጣጫ እንዲለዩ ማድረግ ።

መምህር! ከክፍል ውስጥ አንድ ተማሪ በማስነሣት ፊቱን ወደ ፀሐይ መውጫ አድርጎ እጆቹን በመዘርጋት አቅጣጫዎችን እንዲለዩ ማድረግ። ይህም ማለት የልጁ

ፊት ለፊት የፀሐይ መውጫ ምስራቅ፣ ከልጁ በስተጀርባ ወይም ፀሐይ መግቢያ ምእራብ መሆኑን፣ በልጁ በቀኝ እጅ በኩል ያለው ደቡብ እና በግራ እጅ በኩል ያለው ደግሞ ሰሜን ብለው እንዲለዩ ማድረግ ። በዚህ መሰረት ተማሪዎች የቤታቸውን አቅጣጫ፣ ትምህርት ቤታቸውን መሰረት በማድረግ እንዲናገሩ ማበረታታት። በተጨማሪ ትምህርት ቤታቸውን የተለያዩ አስፈላጊ የሆኑ መስሪያ ቤቶችንና የንግድ ተቋማትን እንዲገልፁና የሚገኙበትን አቅጣጫ እንዲያመለክቱ በማድረግ ትምህርቱን መቋጨት።

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- ስእሎች
- በእንጨት የተሰሩ አቅጣጫን የሚያመለክቱ ሞዴሎች

ግምገና ምዘና /ግምገማና ክትትል/

- አቅጣጫዎችን ለይተው እንዲናገሩ የቃል ጥያቄ መጠየቅ።

- በትምህርት ቤታቸው ግቢ ውስጥ ያሉትን ሕንፃዎች፣ ሽንት ቤቶች፣ ቤተመጽሐፍ፣ ወዘተ. አቅጣጫዎችን እንዲያመለክቱና እንዲናገሩ መጠየቅ።

የመልመጃ **4.1.** መልሶች

1. ሐ
2. ለ
3. ሐ

**4.2.** በአካባቢያችን የሚገኙ ሕይወት የሌላቸው ነገሮች

የተመደበለት ክፍለ ጊዜ 9

ዝርዝር አላማዎች

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፦

- ሕይወት የሌላቸውን ነገሮች ባሕርያት ይዘረዝራሉ።
- ሕይወት ለሌላቸው ነገሮች ምሳሌዎች ይሰጣሉ።
- ሕይወት የሌላቸውን ነገሮች ይሰበስባሉ፣ ያመለክተሉ፣ በአይነታቸውም ይመድባሉ።

ዝርዝር ይዘት

ሕይወት የሌላቸው ነገሮች ባሕሪያት

ሕይወት የሌላቸው ነገሮች ምድብ

የማስተማር መማር ዘዴዎች

መምህር በመጀመሪያ ተማሪዎች ሕይወት ያላቸው ነገሮች የተፈጥሮ ሀብት መሆናቸውን መግለጽ ይኖርብዎታል። ሕይወት የሌላቸው ነገሮች የሚለዩባቸውን ባሕሪያት በውይይት እንዲዘረዝሩ ማድረግና በተማሪዎች ያልተሟላውን በማሟላት ተማሪዎች ያነሷቸውን ነጥቦችና ሃሳቦች በማጠቃለል መግለጽ። ተማሪዎች ከክፍል ውጪ /መስክ/ ወጥተው ሕይወት የሌላቸውን ነገሮች እንዲሰበስቡ የተወሰነ ደቂቃ በመስጠት ተመልሰው ክፍል እንዲገቡ በማድረግ በመሰላቸው መንገድ /በቀለም፣ በመጠን፣ በቅርጽ፣ በክብደት፣ ወዘተ./ እንዲመድቡ ማድረግ ትምህርቱን ይበልጥ ተጨባጭ ያደርገዋል።

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- ሕይወት የሌላቸው ነገሮች /ውሃ፣ አፈር፣ አየር፣ ድንጋይ፣ ወዘተ/
- ስእሎች
- ሞደሎች

ግምገማና ምዘና /ግምገማና ክትትል/

- ሕይወት የሌላቸውን ነገሮች ምሳሌ እንዲጠቅሱ መጠየቅ።
- ሕይወት የሌላቸውን ነገሮች ባሕርያት እንዲዘረዝሩ መጠየቅ።
- ተማሪዎች ሕይወት የሌላቸውን ነገሮች ሰብስበው ሲመድቡ ክትትል ማድረግ።

አየር

ዝርዝር አላማዎች

- አየር መኖሩን ያሳያሉ።
- የአየር ጥቅምን ይናገራሉ።
- አየርን እንዴት መንከባከብ እንዳለባቸው ያሳያሉ።

ዝርዝር ይዘት

- የአየር መኖር
- የአየር ጥቅም

የማስተማሪያ መማሪያ ዘዴዎች

መምህር! ለተማሪዎች የአየር መኖርን ቀላል የሆነ ሙከራ በማሳየት እንዲረዱ ማድረግ ያስፈልጋል። ከመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ካለው ተግባራዊ ክንዋኔ በተጨማሪ በቀርከሃ ወይም በእስክሪፕቶ ቀፎ በውሃ ውስጥ በተንፈስ የሚወጣውን አረፋ በማየት አየር መኖሩን ማረጋገጥ ይቻላል።

እንጨት ጫፍ ላይ ወረቀት በእስፒል በማያያዝ የእንጨቱን እጀታ ይዞ ወደታች በማድረግ ወረቀቱ ጫፍና  ጫፍ ወደታች ሲጐበጥ በማየት በአየር ግፊት ምክንያት ወረቀቱ መጉበጡን እንዲለዩ ማድረግ። በተጨማሪ የተለያዩ ሙከራዎችን እንዲያደርጉ ማበረታታት። አየር ሕይወት ላላቸው ነገሮች አስፈላጊ እንደሆነ በመንገር የአካባቢ አየር እንዳይበከል የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም የአየርን ብክለት መከላከል እንደሚቻል በመግለጽ ትምህርቱን መቋጨት ይኖርብዎታል።

የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

- ብርጭቆ፣ ሻማ፣ ክብሪት፣ እስፒል፣ ፕላስቲክ፣ ጠረጴዛ
- ቀርከሃ ወይም የእስክሪፕቶ ቀፎ
- በአፈር የተሞሉ ጣሳዎች ውስጥ ችግኞች ተተክለው።

ግምገማና ምዘና /ግምገማና ክትትል/

- የአየር መኖርን በተግባራዊ ክንዋኔ ሲሰሩ የተመለከቱትን እንዲናገሩ መጠየቅ።
- የአየርን ጥቅም እንደዘረዝሩ መጠየቅ
- አየር እንዳይበከል /ከብክለት የምንከላከልበትን/ ዘዴዎች እንዲዘረዝሩ መጠየቅ።

ውሃ

ዝርዝር አላማዎች

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፡-

- የውሃ መገኛወችን ይዘረዝራሉ።
- የውሃን ጥቅም ይናገራሉ።
- ውሃን ከብክለት እንዴት መጠበቅ እንዳለባቸው ይናገራሉ።

ዝርዝር ይዘት

- የውሃ ጥቅም
- የውሃ መገኛ
- ውሃን መንከባከብ

የማስተማር መማር ዘዴዎች

መምህር! ተማሪዎች የውሃ መገኛዎችን እንዲዘረዝሩ በማወያየት በተማሪዎች ያልተጠቀሱ ካሉ በማከል መግለጽ። ውሃ ከኩሬ፣ ከወንዝ፣ ከጉድጓድ፣ ከምንጭ፣ ከዝናብ፣ ከቧንቧና ከመሳሰሉት እንደሚገኝ መግለጽ። ውሃ ሕይወት ላላቸው ነገሮች እጅግ አስፈላጊ በመሆኑና በሕይወት እንዲቆዩ ሊያደርጋቸው የሚችሉ መሆኑን በአጽንኦት መግለጽ። በተጨማሪ ውሃ ለመጠጥና ምግብ ማዘጋጀ፤ ንጽሕናን ለመጠበቅ፣ ለእርሻ ሥራ /መስኖ/ ለመሳሰሉት ነገሮች አገልግሎት እንደሚውል ማብራራት። ውሃ በተለያዩ መንገዶች እንደሚበከል እነሱም ከፋብሪካ የሚወጡ አስፈላጊ የሆኑ ኬሚካሎችና ፍሳሾች፤ ከተለያዩ ከመኖሪያ ቤቶች የሚወጡ ቆሻሻዎች፣ በወንዝ ዳር በመፀዳዳት፣ ከብቶችን ወንዝ ውስጥ በማጠብ፣ ልብስን በወንዝ ዳር በማጠብ ይህም የወንዙን ውሃ ንጽሕና እንደሚበከል በማስረዳትና እነዚህም ድርጊቶች እንዳይደረጉ መግለጽ። የተበከለ ውሃን እንዴት ንጽሕናውን ጠብቀን መጠቀም እንደምንችል ለምሳሌ ፡- ውሃን በማፍላት፣ በማጣራት፣ የውሃ እቃዎችን ከድኖ በመጠቀም የውሃን ንጽሕና የመጠበቅ ዘዴንና አስፈላጊነት በመዘርዘር ማስረዳትና ትምህርቱን ማጠቃለል።

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- የቧንቧ ውሃ የጉድጓድ ውሃ፣ የኩሬ ውሃ፣ ወዘተ . ከእውነታው መረጃ በማሳየት
- ስእሎች

ግምገማና ምዘና /ግምገማና ክትትል/

- የውሃ መገኛዎችን እንዲዘረዝሩ መጠየቅ።
- የውሃ ጠቀሜታ ምን ምን እንደሆነ እንዲገልፁ መጠየቅ።
- የውሃን ንጽሕና እንዴት እንደምንጠብቅ የቃል ጥያቄ መጠየቅ።

አፈር

ዝርዝር አላማዎች

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፡-

- የአፈርን አይነት በቅርፃቸውና በቀለማቸው ይለያሉ።
- የአፈርን ጥቅምን ይዘረዝራሉ።
- አፈርን እንዴት መንከባከብ እንዳለብን ይዘረዝራሉ።

ዝርዝር ይዘት

- የአፈር አይነት
- የአፈር ጥቅም
- የአፈር እንክብካቤ

የማስተማር መማር ዘዴዎች

መምህር! ተማሪዎች የተለያዩ የአፈር አይነቶችን በቅርጽ ስንለይ አሸዋማ፣ ደቃቅና የሸክላ አፈር መኖራቸውን በማብራራት አፈር የተለያየ ቀለማት አለው። ይኸውም ጥቁር፣ ቀይ እና ዳለቻ መሆናቸውን ለማስገንዘብ ይረዳ ዘንድ ተማሪዎች እነዚህን የአፈር አይነቶች ከሚገኙበት አካባቢ እንዲያሰባስቧቸው የቤት ስራ በመስጠት የተሰበሰቡትንም የአፈር አይነቶች በቀለማቸው በመመደብ በላስቲክ ውስጥ በማድረግና በካርቶን ላይ በስፒል አያይዞ ክፍል ውስጥ በመስቀል ተማሪዎች ለናሙናነት እንዲመለከቱት ማድረግ። በመቀጠልም የአፈርን ጥቅም በሚመለከት ተማሪዎች እንዲወያዩ በማድረግና የተወያዩበትን ሃሣብ በመውሰድ አፈር ለቤት መስሪያነት፣ እጽዋትን ቀጥ ብሎ እንዲቆምና ለእጽዋት ምግብነትና ከሸክላ አፈር የተዘጋጀ ጭቃ በማዘጋጀትና የተለያዩ ጌጣጌጦችን የቤት ቁሳቁሶችን ሞዴሎች ሰርተው እንዲያሳዩ በማድረግ። የአፈርን ጥቅም እንዲለዩ ማድረግ። አፈርን በጐርፍ ውሃ ታጥቦ እንዳይወሰድ የዛፍ ችግኝ በመትከል፣ በኩብቶች ሳሩ ከመጠን በላይ እንዳይጋጥ በማድረግ አግድም በማረስና በተለያዩ መንገዶች አፈርን መንከባከብ እንደሚቻል ማብራራት።

የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

- የተለያዩ የአፈር አይነቶች
- ከሸክላ አፈር የተሰሩ ልዩ ልዩ እቃዎች /ሞዴሎች/
- የተዘጋጀ የሸክላ አፈር ጭቃ

ግምገማና ምዘና /ግምገማና ክትትል/

- ተማሪዎች ከአፈር የተለያዩ ቁሳቁሶች እንዲሰሩ ክትትል ማድረግ።
- የአፈርን ጥቅም እንዲዘረዝሩ መጠየቅ።
- የአፈር አይነቶችን ከአካባቢያቸው እንዲያመጡ በማድረግና በቅረፃቸውና በቀለማቸው እንዲለዩ ክትትል ማድረግ
- አፈርን እንዴት መንከባከብ እንደሚችሉ መጠየቅ።

የመልመጃ **4.2.** መልሶች

ሀ. 1. ሐሰት

2. እውነት

3. እውነት

4. ሐሰት

5. እውነት

ለ. 6. ለ

7. ሐ

8. ሐ

9. ሀ

10. ሐ

**4.3.** በአካባቢያችን የሚገኙ ሕይወት ያላቸው ነገሮች

የተመደበለት ክፍለ ጊዜ ብዛት 9

ዝርዝር አላማዎች

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፦

- ሕይወት ያላቸው ነገሮች በሁለት የሚከፈሉ መሆናቸውን ይለያሉ።
- ሕይወት ያላቸውን ነገሮች ባሕርያት ይዘረዝራሉ።

ዝርዝር ይዘት

ሕይወት ያላቸው ነገሮች ምድብ

- እንስሳት
- እጽዋት

ሕይወት ያላቸው ነገሮች ባሕሪያት

የማስተማር መማር ዘዴዎች

መምህር ተማሪዎች በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢና ከትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውጪ የእግር ጉዞ በማድረግ ሕይወት ያላቸው ነገሮች ምድባቸውን እንዲለዩ ማድረግ፤ ማለትም እንስሳትና እጽዋት በማለት በተጨማሪ ሕይወት ያላቸው ነገሮች ከሌላቸው ነገሮች በምን በምን

ባሕሪያት እንደሚለዩና እንደሚመሳሰሉ በክፍል ውስጥ በውይይት ማዳበር እንዲችሉ ማበረታታት። ይህም የሚመሳሰሉበትን ሁሉንም የተፈጥሮ ሀብት መሆናቸውንና ለሰው ልጅ ሕይወት መራዘም የሚረዱ መሆናቸውን እንዲሁም እርስ በእርስ ጥብቅ ትስስር እንዳላቸው መግለጽ። የሚለየዩበት ደግሞ ሕይወት ያላቸው ነገሮች ሲተነፍሱ ሕይወት የሌላቸው እንደማይተነፍሱ፤ ሕይወት የሌላቸው እንደማይራቡና እንደማይመገቡ ሕይወት ያላቸው ነገሮች ግን መራባትና መመገብ እንደሚችሉ በማብራራት ትምህርቱን መቋጨት።

የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

- ሕይወት ያላቸውንና የሌላቸውን ነገሮች ተዘዋውረው በማየት በእውን መረጃ በማነፃፀር መጠቀም።
- ስእሎች /ከመማሪያ መጽሐፍ ሥእል 4.22 ፣ 4.23፣ 4.24 እና 4.25 ን ይመልከቱ/
- ፎቶግራፎች

ግምገማና ምዘና /ግምገማና ክትትል/

- ተማሪዎች በመስክ ጉብኝት ያዩትን ሕይወት ያላቸውንና የሌላቸውን እንዲለዩ መጠየቅ።
- ሕይወት ያላቸው ነገሮች ባሕርያት ምን ምን እንደሆነ መጠየቅ

እጽዋት

የእጽዋት ምደባ

ዝርዝር አላማዎች

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፡-

- ዛፎች፣ ቁጥቋጦዎችና ትናንሽ እፅዋት፣ትላልቅና ትናንሽ ሳሮች በማለት ይመድባሉ።
- የሚበሉና የማይበሉ የእጽዋት አይነትን ይለያሉ።
- የእጽዋትን ዋና ዋና ክፍሎች ይናገራሉ።

ዝርዝር ይዘት

- እጽዋትን መመደብ

- ለምግብነት የሚውሉ
- ለምግብነት የማይውሉ
- የእጽዋት ዋና ዋና ክፍሎች

የማስተማር መማር ዘዴዎች

መምህር! ተማሪዎች በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢና ከትምህርተ ቤት ቅጥር ግቢ ውጪ የእግር ጉዞ በማድረግ የተለያዩ እጽዋቶችን እንዲመለከቱና እንዲመድቡ ማድረግ። ምድባቸውም ትልልቀ ዛፎች፣ ቁጥቋጦዎችና ትናንሽ ዛፎች፣ ረጃጅምና አጫጭር ሳሮች በማለት እንዲመድቡ ማድረግ። በተጨማሪ እጽዋት በሁለት ክፍል እንደሚመደቡ እነሱም ለምግብነት የሚውሉ እና ለምግብነትየማይውሉ መሆናቸውን የእጽዋቶችንም አይነት በመዘርዘር ከመማሪያ መጽሐፍ ላይ ሥእሎቻቸውን በማሳየት እንዲለዩ ማድረግ። /ሥእል 1.28 / የእጽዋት ዋና ዋና ክፍሎች የሚባሉት ሥር፣ ግንድ፣ ቅጠልና ቅርንጫፍ መሆናቸውን ስዕሉን በማሳየት የእያንዳንዱን የእጽዋት ክፍል እራሳቸው ተማሪዎቹ እንዲያሳዩና ከአፈር በታችና ከአፈር በላይ ያለውን የእጽዋት ክፍል በመለየት እንዲናገሩ ማድረግ።

የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

- ስእሎች /ለምግብነት የሚውሉና የማይውሉ ከመማሪያ መጽሐፍ ሥእል 4.28 ይመልከቱ/
- ፎቶግራፎች
- እውን መርጃ /ዛፎችን/

ግምገማና ምዘና / ግምገማና ክትትል/

- ተማሪዎች በመስክ ጉብኝታቸው ያዩዋቸውን የእፅዋት አይነቶች በምድባቸው ለይተው እንዲናገሩ መጠየቅ።
- የሚበሉ እና የማይበሉ እጽዋትን እንዲዘረዝሩ መጠየቅ።
- የእጽዋት ዋና ዋና ክፍሎችን በስእል ለይተው እንዲያሳዩ መጠየቅ።

የእጽዋት ጥቅም

ዝርዝር አላማዎች

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፦

- የእጽዋትን ጥቅም ይዘረዝራሉ።
- ለምግብነት የሚውሉና የማይውሉትን የእፀዋት ጥቅም ይለያሉ።
- የእፅዋትን መለያ ባሕርያት ይለያሉ።

ዝርዝር ይዘት

- የእፀዋት ጥቅም
    - ለምግብነት
    - ለቤት ቁሳቁስ መስሪየ
    - ልብስ ለመስራት
    - ለእንስሳት መጠለያነት

- የእፀዋት መለያ ባሕሪያት

የማስተማር መማር ዘዴዎች

መምህር! ተማሪዎች እጽዋት ለምን ለምን እንደሚጠቅሙ ተራ በተራ መግለጫ እንዲሰጡና በግላቸውም ለምግብነት፣ ለቤት መስሪየና ለቤት ቁሳቁስ መስሪያነት፣ ልብስ ለመስራት፣ ለእንስሳት መጠለያነት፣ ለግቢ ውበት እንደሁም ለማገዶነት ብለው እንዲዘረዝሩ ማበረታታት። በተጨማሪም ለምግብነት የሚውሉ እጽዋት አትክልትና ፍራፍሬ፣ የሰብሎች ወይም የእህልና ጥራጥሬ ተብለው እንደሚመደቡ እና ልብስ ለመስራት ሲባል ከጥጥ ተክል እስከ ልብስ ሆኖ እስኪወጣ ያለውን በባሕላዊም ሆነ በዘመናዊ የእደጥበብ ሥራ ሂደት በመዘርዘር እጽዋት እንዴት ለልብስ መስሪያነት እንደሚጠቅም በዝርዝር ማስረዳት።

መምህር! ስለ እጽዋት መለያ ባሕሪያት እንዲለዩ ፦ ለምሳሌ እጽዋት ይራባሉ፣ ያድጋሉ፣ ይመገባሉ፣ ወዘተ በማለት ከመማሪያ መጽሐፍ /ሥእል 4.37 ፣ 4.38 እና 4.39 ን ይመልከቱ/ በመጨረ ሻ በክለሳ ትምህርቱን መቋጨት።

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- ስእሎች
- ፎቶግራፎች
- ከእጽዋት የተሰሩ ቁሳቁሶች

ግምገማና ምዘና /ግምገማና ክትትል/

- የእጽዋትን ጥቅም እንዲዘረዝሩ መጠየቅ።
- ለምግብነት የሚውሉና ለምግብነት የማይውሉ እጽዋት ጥቅም ለይተው እንዲናገሩ መጠየቅ።
- የእጽዋትን መለያ ባሕርያት እንዲዘረዝሩ መጠየቅ።

የእጽዋት እንክብካቤ

ዝርዝር አላማዎች

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፡-

- እጽዋትን እንዴት መንከባከብ እንዳለባቸው ይዘረዝራሉ።
- አካባቢያቸውን እንዴት በእጽዋት ማልማት እንዳለባቸው ይናገራሉ።

ዝርዝር ይዘት

- የእጽዋት እንክብካቤ
    - ውሃ ማጠጣት
    - ማረም
    - ማዳበሪያ መጨመር
    - በእንስሳት እንዳይበሉ መጠበቅ

የማስተማር መማር ዘዴዎች

መምህር! ተማሪዎች በአካባቢያቸው እጽዋትን እንዴት መንከባከብ እንዳለባቸው ማለትም ተክሉ ከተተከለ ጊዜ ጀምሮ ውሀ በማጠጣት፣ በማረምና በመኮትኮት ማዳበሪያ በመጨመር፣ በእንስሳት እንዳይበሉ መጠበቅ እንዳለባቸው ማስረዳት። እጽዋትን ካልተንከባከብናቸው እንደሚሞቱ በተጨማሪ እጽዋትን ያለአግባብ መቅጠፍ ወይም መቁረጥ ተገቢ እንዳልሆነ በመግለጽ ተማሪዎች አካባቢየቸውንም ሆነ ትምህርት ቤታቸውን በአረንጓዴ ተክሎች እንዲሸፍኑ /እንዲያለሙ/ በመንገር ትምህርቱን መቋጨት።

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- ስእሎች /ከመማሪያ መጽሐፍ ሥእል 4.40 ይመልከቱ/

- ፎቶግራፎች

ግምገማና ምዘና /ግምገማና ክትትል/

- እጽዋትን እንዴት መንከባከብ እንዳለባቸው እንዲዘረዝሩ መጠየቅ።
- አካባቢበያቸውን በአረንጋደ ተክሎች እንዴት ማልማት መሸፈን እንደሚገባቸው መጠየቅ።

እንስሳት

የእንስሳት አመዳደብ

ዝርዝር አላማዎች

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፡-

- እንስሳትን ለማዳ እና የዱር በማለት ይለያሉ።
- ለማዳና የዱር እንስሳትን በመለየት ይዘረዝራሉ።
- ለማዳና የዱር እንስሳትን መኖሪያቸውን ይገልጻሉ።

ዝርዝር ይዘት

- የቤት እንስሳት
- የዱር እንስሳት

የማስተማር መማር ዘዴዎች

መምህር! ተማሪዎች እንስሳትን የቤት /ለማዳ/ እና የዱር በማለት እንዲለዩ የሚያውቋቸውን የዱር እንስሳቶች እና የቤት እንስሳቶችን እንዲዘረዝሩ በመጠየቅ ትምህርቱን መጀመር። ተማሪዎች ከሰጡት ዝርዝር በመነሳት ሥእሎችን እያመለከቱ የዱር እንስሳቶች ማን ማን እንደሆኑና የት እንደሚኖሩ እንዲሁም የቤት እንስሳት /ለማዳ/ የምንላቸውን ስእሎችን እያመለከቱና የት እንደሚኖሩ እንዲናገሩ በማድረግ ትምህርቱን መቋጨት።

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- ስእሎች /ከመማሪያ መጽሐፍ ሥእል 4.41 ይመልከቱ/
- ፎቶግራፎች

ግምገማና ምዘና /ግምገማና ክትትል/

- እንስሳትን በምድባቸው ለይተው እንዲናገሩ መጠየቅ።
- የዱር እንስሳት ማን ማን እንደሆኑ ሥእል በማመልከት እንዲዘረዝሩ መጠየቅ።
- የቤት /ለማዳ/ እንስሳትን ማን ማን እንደሆኑ ሥእል በማመልከት እንዲዘረዝሩ መጠየቅ።

የእንስሳት አልግሎት

ዝርዝር አላማዎች

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፡-

- የእንስሳትን አገልግሎት ይናገራሉ።
- የቤት እንስሳትንና የዱር እንስሳትን አገልግሎት ለይተው ይናገራሉ።

ዝርዝር ይዘት

- የቤት /ለማዳ/ እንስሳት ጥቅም
- የዱር እንስሳት ጥቅም

የማስተማር መማር ዘዴዎች

መምህር! የእንስሳትን ጥቅም ምን ምን እንደሆነ በመጠየቅ ይጀምሩ። ከተማሪዎች መልስ በመነሳት የእንስሳት ጥቅም ለምግብነት፣ ለጥበቃ፣ ዕቃ ለማጓጓዣነት ለልብስና ለጫማ መስሪያ የሚያገለግሉ መሆኑን መግለጽ። በተጨማሪ የዱር እንስሳት በተፈጥሮ ውበታቸው ለቱሪዝም መስእብነትና ለገቢምንጭ ማስገኛነት የሚያገለግሉ መሆናቸውን መግለጽ። በሀገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ የሚገኙ አእዋፋትና ብርቅዬ እንስሳትን በስእሎች በማስደገፍና የሚገኙበትን ቦታ ጭምር መንገር። እንዲሁም ለማዳ የሆኑ እንስሳት ለመጓጓዣነት፣ ለቤት ጥበቃ የሚያገለግሉትን ለይተው እንዲያውቁ ማብራራት። የእንስሳት ቀንድ ለጌጣጌጥ ለቤት መገልገያ ቁሳቁስ መስሪያነት ፀጉራቸው ደግሞ ለልብስ መስሪያነት ምሳሌ የበግ ፀጉር ለብርድ ልብስ፣ ለኮትና ለሱሪ መስሪያነት እንደሚውል በማብራራት ትምህርቱን መቋጨት።

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- ስእሎች

- ሞዴሎች
- ፎቶግራፎች

ግምገማና ምዘት /ግምገማና ክትትል/

- የእንስሳትን አገልግሎት ምን ምን እንደሆኑ እንዲናገሩ መጠየቅ።
- የቤት እንስሳት ጥቅማቸውን ለይተው እንዲዘረዝሩ መጠየቅ።
- የዱር እንስሳት ለምን ለምን እንደሚጠቅሙ በመለየት እንዲናገሩ መጠየቅ።

የእንስሳት እንክብካቤ

ዝርዝር አላማዎች

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፡-

- እንስሳትን እንዴት መንከባከብ እንዳለባቸው ያስረዳሉ።
- የቤት እንስሳትና የዱር እንስሳትን እንክብካቤ ለይተው ይገልጻሉ።
- የእንስሳትን ባሕርያት ይለያሉ።

ዝርዝር ይዘት

- የቤት እንስሳትን መንከባከብ
- የዱር እንስሳትን መንከባከብ

የማስተማር መማር ዘዴዎች

መምህር! የቤት እንስሳት ባለቤት በምንሆንበት ጊዜ የሚከተሉትን ተግባራት መፈፀም አስፈላጊ እንደሆነ በመንገር ትምህርቱን መጀመር ። ይህም ምግብን መመገብ፣ ውሃ ማጠጣት፣ መጠለያ ማዘጋጀት ከጭካኔ አያያዝ ውጪ መያዝ የመሳሰሉት እንደሆኑ መግለጽ። የዱር እንስሳት ከላይ የተዘረዘሩትን በራሳቸው የሚያገኙ ቢሆንም አካባቢያቸውን እኛ መጠበቅና መንከበከብ እንዳለብን መንገር። ስለዚህ የቤት እንስሳትን መንከባከብ እንጂ ማሰቃየት ተገቢ እንዳልሆነ መግለጽ። የእንስሳት መለያ ባሕሪያት፡- እንደሚዋለዱ፣ እንደሚተነፍሱ፣ እንደሚንቀሳቀሱና እንደሚመገቡ ማስረዳት። እንስሳት የሚራቡት እንቁላል በመጣል ወይም መሰላቸውን በመውለድ እንደሆነ ማስረዳት ያስፈልጋል። የሚተነፍሱባቸው የሰውነት ክፍሎች የተለያዩ መሆናቸውን፤ ከቦታ ቦታ ምግብ ፍለጋና መኖሪያ ፍለጋ እንደሚንቀሳቀሱ መንገርና ትምህርቱን መቋጨት።

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- ስዕሎች /ከመማሪያ መጽሐፍ ሥእል 4.49 ይመልከቱ/
- ፎቶግራፎች

ግምገማና ምዘና /ግምገማና ክትትል/

- እንስሳትን እንዴት መንከባከብ እንዳለባቸው በዝርዝር እንዲገልጹ መጠየቅ።
- የቤት እንስሳትና የዱር እንስሳት ጥቅም ለይተው እንዲናገሩ መጠየቅ።
- የእንስሳትን መለያ ባሕርያት እንዲዘረዝሩ መጠየቅ።

የመልመጃ **4.4** መልሶች

ሀ. 1. ሐሰት
2. እውነት
3. እውነት
4. ሐሰት
5. ሐሰት

ለ. 6. ሐ
7. ለ
8. ሀ
9. ሐ
10. ሐ

ሐ. 11. ምግብና መኖሪያ ለመፈለግ
12. የቤት /ለማዳ/ እንስሳት

**4.4.** በአካባቢያችን የሚደረጉ የተለመዱ እንቅስቃሴዎች

የተመደበለት ክፍለ ጊዜ ብዛት 13

የስራ ጥቅም

ዝርዝር አላማዎች

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፦

- የሥራን ጥቅም ይናገራሉ።
- ስራ መሰረታዊ ፍላጐትን ለማማላት አስፈላጊ መሆኑን ይገልፃሉ።

- ሥራ ኑሮን በአግባቡ ለመምራት አስፈላጊ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

ዝርዝር ይዘት

- የሥራ ጥቅም
    - መሠረተዊ ፍላጐትን ለማሟላት
    - ኑሮን በሥራ መምራት

የማስተማር መማር ዘዴዎች

መምህር! ሥራ መሰረተዊ ፍላጐትን ለማሟላት ኑሮን በአግባቡ ለመምራት አካባቢንና ሀገርን ለማልማት አስፈላጊ መሆኑን ማስገንዘብ፡፡ ይህም ሊሆንየሚችለው ሰዎች ሥራን ሳይንቁ ተግተውና ጥረው ሲሰሩ ብቻ መሆኑን በዝርዝር መግለጽ፡፡ ተማሪዎችን ወላጆቻቸው ገንዘብ ማግኘት ባይችሉ ኖሮ ምን እንደሚፈጠር መጠየቅ፡፡ ኑሮዋቸው እንዴት ሊሆን እንደሚችል እንዲያስረዱ በማበረታታት ትምህርቱን መቋጨት፡፡

የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

- እውን መረጃ /በአካባቢያቸው ስራን የሚሠራ ቤተሰብንና ሥራን የማይሰራ ቤተሰብን በማነፃፀር ማስረዳት/
- ስእሎች

ግምገማና ምዘና /ግምገማና ክትትል/

- የስራን አስፈላጊነት እንዲዘረዝሩ መጠየቅ፡፡
- ሥራ ኑሮን ለመምራት አካባቢን ለማልማት አስፈላጊነትን እንዲገልፁ የቃል ጥያቄ መጠየቅ፡፡

የስራን አይነቶች መመደብ

ዝርዝር አላማዎች

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፡-

- የሥራን የተለያዩ ምድቦች ይናገራሉ፡፡
- ሥራን የመንግሥትና የግል በማለት መድበው ይዘረዝራሉ፡፡
- በከተማና በገጠር ያሉትን የሥራ አይነቶች ይለያሉ

ዝርዝር ይዘት

- የሥራ አይነቶች ምደባ
  - የግል ሥራ
  - የመንግሥት ሥራ
  - ለሰዎች ተቀጥሮ መስራት

የማስተማር መማር ዘዴዎች

መምህር! ተማሪዎች ልዩ ልዩ የሥራ አይነቶች ከሚከናወኑባቸው አካባቢዎች ስለሚመጡ ወላጆቻቸውና የአካባቢው ሕብረተሰብ ምን አይነት ሥራን እንደሚሰሩ በመወያየት ትምህርቱን መጀመር። የስራ አይነቶች ሲመደቡ የግል ሥራ፣ ለሌሎች ሰዎች ተቀጥሮ መስራት፣ ለመንግሥት ተቀጥሮ መስራት ተማሪዎች ለእነዚህ የተለያዩ ሥራዎችን እንዲመድቡ ማድረግ። በተጨማሪም ተማሪዎቹን ስለወላጆቻቸው ሥራ በመጠየቅ መመደብና ማሳየት። ሰዎች በግል ሥራ ሊሰማሩ የሚችሉትን በግብርና፣ በንግድ፣ በሽመና፤ በሸክላ ሥራና በመሳሰሉት መሆናቸውን መግለጽ።

መምህር በዘመናዊ የግብርና አስተራረስ ዘዴ ሰፋፊ ቦታዎች በማልማት ጥቅም ላይ አውሎ ረሀብና ችግርን ከሀገራችን ማጥፋት እንደሚቻል በመግለጽ ትምህርቱን መቋጨት።

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- ስእሎች /ከመማሪያ መጽሐፍ ሥእል 4.50፣ 4.51፣ 4.52፣ 4.53፤ 4.54፤ 4.55፤ 4.56፤ 4.57 ፤ 4.58 ን ይመልከቱ /
- ፎቶግራፎች

ግምገማና ምዘና /ግምገማና ክትትል/

- የመንግሥትና የግል ሥራን ለይተው እንዲዘረዝሩ መጠየቅ።
- የተለያዩ የሥራ ምድቦችን እንዲናገሩ መጠየቅ።
- በአካባቢያቸው ምን ምን አይነት ሥራ እንደሚሰራ መጠየቅ።

የሥራ ክቡርነት

ዝርዝር አላማዎች

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፡-

- የስራ ክቡርነትን በሚሰጣቸው አነስተኛ ትእዛዝ በተግባር ያሳያሉ።
- የጊዜን ጠቀሜታ ይገልጻሉ።
- ሥራን በእቅድ መምራት አስፈላጊነት ይናገራሉ።

ዝርዝር ይዘት

የሥራ ክቡርነት

- ጊዜን በአግባቡ መጠቀም
- ሥራን በእቅድ መምራት

የማስተማር መማር ዘዴዎች

መምህር! ተማሪዎች ማንኛውም ሥራ የተከበረ መሆኑን እንዲያውቁ ማድረግ።

ለምሳሌ የሽመና ሥራ ሸማኔ የተለያዩ ልብሶችን ሰርቶ ሰዎችን በማልበስ ጥቅም እንደሚሰጥና ሥራውም የተከበረ መሆኑን ማብራራት። እንዲሁም ሌሎች የሥራ /የሙያ/ አይነቶች እንደ ሸክላ ሥራ ፣ የእርሻ ሥራ፣ ንግድና የመሳሰሉት እንደሆኑ ለሁሉም አይነት ሥራ ክብር መስጠት እንደሚገባን መግለጽ።

መምህር! የጊዜ ጠቀሜታ በተመለከተ በጥያቄና መልስ ማወያየት። የሥራ ሰአትን ማክበር። ከትምህርት ውጪ ያሉትን ጊዜያት ለጥናት፣ ለጨዋታና ቤተሰብን ለመርዳት ጊዜን በእቅድ ከፋፍሎ መጠቀም አስፈላጊ መሆኑን በዝርዝር ማወያየትና ማስረዳት። ተማሪዎች በዚህ እድሜያቸው ሰአትን ማክበር ልምዳቸው /ባሕላቸው/ አድርገው እንዲያድጉ ስለሚያስፈልግ በተለያዩ ዘዴዎች ማስረዳት። በተቃራኒው ማርፈድና ጊዜን በአልባሌ ሥፍራ ማሳለፍ የማይደገፉ ሁኔታዎች መሆናቸውን ማስገንዘብ ሰንጠረዥ 4.2 ጊዜ ሳይባክን በእቅድ ከፋፍሎ መጠቀም የሚለውን ተማሪዎች በአንድ ገጽ ወረቀት ላይ እንዲገለብጡ በማድረግና ወደ ቤታቸው በመውሰድ ከወላጆቻቸው ጋር በመመካከር ጊዜያቸውን በአግባቡ ከፋፍለው እንዲጠቀሙ በማድረግ ትምህርቱን መቋጨት።

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- ስእሎች /ከመማሪያ መጽሐፍ ሥእል 4.59፤ 4.6 ዐን ይመልከቱ/
- ፎቶግራፎች

ግምገማና ምዘና /ግምገማና ክትትል/

- ተማሪዎች የሥራ ክቡርነት በሚሰጣቸው አነስተኛ ትእዛዝ መተግበራቸውን መከታተል።
- የጊዜን ጠቀሜታ እንዲገልጹ መጠየቅ።

የመልመጃ **4.5** መልሶች

ሀ. 1. እውነት

2. ሐሰት

3. ሐሰት

ለ. 4. ለ

5. ለ

## **4.5.** መጓጓዣዎች

የተመደበበት ክፍለ ጊዜ ብዛት 13

ባሕላዊ መጓጓዣ

ዝርዝር አላማዎች

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፦

- ባሕላዊ መጓጓዣዎችን ይለያሉ።
- የባሕላዊ መጓጓዣዎች ውስጥ ከሚሰጡት ጥቅም አንፃር ያነፃጽራሉ።

ዝርዝር ይዘት

ባሕላዊ መጓጓዣ

- የእግር ጉዞ
- ፈረስ
- አህያ
- ግመል

የማስተማር መማር ዘዴዎች

መምህር! ባሕላዊ መጓጓዣዎች ተብለው የሚመደቡት የእግር ጉዞ፣ በፈረስ መጓዝ፣ በአህያና ግመል መጓዝ ናቸው። ለተማሪዎች የተለያዩ የመጓጓዣ አይነቶችን በፎቶግራፍ ወይም በስእል በማሳየት እንዲያውቋቸው ማድረግ። በፎቶ ወይም በስእል ያዩዋቸውን በተለያየ አካባቢ እንዲያዩዋቸው ማበረታታት። ተማሪዎች የሚያውቋቸውንና የሚወዱዋቸውን የተጓዙበትን ሁኔታ በጨዋታ መልክ እንዲያቀርቡ ማበረታታት። ይኸውም ከቤተሰቦቻቸው ጋር ራቅ ያሉ ቤተሰቦቻቸውን ለመጠየቅ ያደረጉት ጉዞ ካለ ተማሪዎች ወጥተው እንዲናገሩ ማድረግ።

የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

- ስእሎች /ባሕላዊ መጓጓዣዎችን የሚያሳይ/
- ፎቶግራፍ

ግምገማና ምዘና /ግምገማና ክትትል/

- ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚገኙ የባሕላዊ መጓጓዣ አይነቶችን እንዲዘረዝሩ መጠየቅ።
- የባሕላዊ መጓጓዣ ስእሎችን ወይንም ፎቶግራፎችን በማሳየት ስማቸውን እንዲጠሩ መጠየቅ።

ዘመናዊ መጓጓዣ

ዝርዝር አላማዎች

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፡-

- ዘመናዊ መጓጓዣዎችን ይለያሉ።
- ከዘመናዊ መጓጓዣዎች ውሰጥ ከሚሰጡት ጥቅም አኳያ ያነፃጽራሉ።

ዝርዝር ይዘት

- ዘመናዊ መጓጓዣ
    - መኪና
    - አውሮፕላን
    - ባቡር
    - መርከብ

- ሳይክል

የማስተማር መማር ዘዴዎች

መምህር! ዘመናዊ የመጓጓዣ አይነቶች መኪና፣ የጭነት መኪና፣ አውቶብስ፣ ባቡር፣ አውሮፕላን፣ መርከብ መሆናቸውን መግለጽ። እነዚህ የመጓጓዣ አይነቶች የሚሄዱባቸውን መንገዶች እንዲለዩ ማድረግ። ይህም አውሮፕላን በአየር ላይ እንደሚሄድ ፣ ባቡር በሐዲድ ላይ እንደሚጓዝ፣ መርከብ በውሃ ላይ እንደሚሄድ በማብራራትና በመካከላቸው ያለውን ልዩነት በግልጽ ትምህርቱን መቋጨት።

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- ስእሎች /ዘመናዊ የመጓጓዣ አይነቶች የሚያሳዩ በመማሪያ መጽሐፍ ሥዕል 4.64ን ይመልከቱ/
- ፎቶግራፍ
- ፓስተሮች

ግምገማና ምዘና /ግምገማና ክትትል/

- ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚገኙ ዘመናዊ የመጓጓዣ አይነቶችን እንዲዘረዝሩ መጠየቅ።
- የዘመናዊ መጓጓዣ ስእሎችን ወይም ፎቶግራፎችን በማሳየት ስማቸውን እንዲጠሩ መጠየቅ።

የመጓጓዣ ጥቅም

ዝርዝር አላማዎች

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፡-

- የመጓጓዣን ጥቅም ይዘርዝራሉ።
- የዘመናዊና የባሕላዊ መጓጓዣ ያወዳድራሉ።

ዝርዝር ይዘት

- የመጓጓዣ ጥቅም

- ምቾት
- ፍጥነት
- ከባድ እቃን ማጓዝዝ

የማስተማር መማር ዘዴዎች

መምህር! ተማሪዎች የመጓጓዣን ጥቅም እንዲዘረዝሩ በመጠየቅ ትምህርቱን መጀመር። ዘመናዊ መጓጓዣ ከባሕላዊ መጓጓዣ ጋር ያለውን ልዩነት እንዲናገሩ በማድረግ የሚሰጡትን ጥቅም እንዲያወዳድሩ ማበረታታት። ባሕላዊ መጓጓዣዎች የሚሰጡት ግልጋሎት መንገዱ ለዘመናዊ መጓጓዣ ያልተመቻቸ ከሆነ ባሕላዊ መጓጓዣ ጠቀሜታው ከፍተኛ መሆኑን መግለጽ። ዘመናዊ መጓጓዣ የሚሰጠው ጥቅም ፍጥነት እንዳለው ብዙና ከባድ እቃዎችን ለማጓጓዝ እንደሚጠቅም ማብራራትና ትምህርቱን መቋጨት ።

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- ስእሎች
- ፓስተሮች
- ፎቶግራፎች

ግምገማና ምዘና /ግምገማና ክትትል/

- ተማሪዎች የመጓጓዣን ጥቅም እንዲገልፁ መጠየቅ።
- የዘመናዊና ባሕላዊ መጓጓዣዎች ጥቅም ልዩነት በማነፃፀር እንዲናገሩ መጠየቅ።

የክለሳ ጥያቄ መልሶች

ሀ. 1. እውነት
2. ሐሰት
3. ሐሰት
4. እውነት
5. እውነት

ለ. 6. ለ

7. መ

8. ሠ

9. ሐ

10. ሀ

ሐ. 11. ሐ

12. ሐ

13. ሐ

14. ለ

15. ሐ